የሰበር ሰበርና ተግዳሮቶቹ በኢትዮጵያ

መሓሪ ረዳኢ*

አህጽሮተ ጽሁፍ

በፌዴራልና በክልል የሥልጣን ክፍፍል ማዕቀፍ ውስጥ የወንጀል፤ የጉምሩክ፤ የንግድና የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነትን የሚመለከቱ ጉዳዮች በፌዴራል መንግሥት የሥልጣን ክልል ሥር የሚገኙ በመሆናቸው በፌዴራሉ ሰበር ሰሚ የሚመረመሩ ናቸው፡፡ ከዚህ ውጭ ያሉት የዕለት ተዕለት የውል፤ የቤተሰብ፤ የውርስና የመሳሰሉት ጉዳዮች ግን የክልል ጉዳዮች ስለሆኑ የፍትሕ አስተዳደራቸው በክልል የዳኝነት ሂደት ላይ ሊያበቃ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ የክልል ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ተክተው ያስተናገዱዋቸውን የፌዴራል ጉዳዮችም ሆነ በክልል የዳኝነት ሥልጣናቸው በሰበር ጭምር አይተው የመጨረሻ እልባት የሰጡባቸውን ክልላዊ ጉዳዮች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአሁኑ ወቅት ዳግም እያከራከረ ይገኛል፡፡ የክልል ሥልጣን በሆነ ጉዳይ፣ የክልል ሕግን መሠረት በማድረግ የክልል ፍርድ ቤቶች የዳኙትንና በክልል ሰበርም ጭምር አይተው የመጨረሻ ውሳኔ የሰጡበትን ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እያስቀረበ ማከራከሩ፣ የሕገ መንግሥቱን ቃላትና መንፈስ መሠረት ያላደረገ፣ እንዲሁም በሕግ ያልተደገፈ መሆኑን ማሳየት የዚህ ጽሁፍ ዋነኛ ጭብጥ ነው፡፡ ይህ አሠራር ይልቁንም የፌዴራል ሕገ መንግሥቱ ያደራጀውን የፌዴራልና የክልሎች የዳኝነት የሥልጣን ክፍፍል ተፈጻሚነት አጠያያቂ የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን የሰበር ሰሚ ችሎቱንም ወደማይወጣው የጉዳዮች ጫና ውስጥ ስለሚከተው ውጤታማነቱን በእጅጉ እንደሚቀንሰው ጽሁፉ ያሳያል፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎቱ አቅሙንና ጊዜውን በእጅጉ በሚሻሙና በአመዛኙ አካባቢያዊ (local) በሆኑ ጉዳዮች መጠመዱ የግብአት ብክነትን ይፈጥርበታል፡፡ የክልል ጉዳያቸውን በራሳቸው ለመዳኘት ክልሎች ባላቸው ሥልጣን ውስጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዳይገባ (hands-off) ጽሁፉ ይጠይቃል፡፡ ይልቁንም የፌዴራሉ የመጨረሻ የዳኝነት አካል የክልል ጉዳዮችን በሰበር በመከለስ ዝርዝር ጉዳይ (micro-management) ሳይጠመድ፣ የክልሎች የዳኝነት አቅም የሚዳብርበትን አቅጣጫ ቢቀይስና በዚሁ የአቅም ግንባታ ሥራ ላይ ቢያተኩር አመርቂ ውጤት እንደሚገኝ ጽሁፉ ይጠቁማል፡፡

ቁልፍ ቃላት

ሰበር፤ የሰበር ሰበር፤ የክልል ጉዳይ፤ የፌዴራል ጉዳይ፤ ሕገ መንግሥት፤ የመጨረሻ ውሳኔ፤ መሠረታዊ የሕግ ስህተት፤ የፌዴራልና የክልል የሥልጣን ክፍፍል፤

DOI http://dx.doi.org/10.4314/mlr.v9i1.6

---

* መሓሪ ረዳኢ፣ ኤል ኤል ቢ(Addis Ababa University-Ethiopia)፣ ኤል ኤል ም (University of Michigan-USA)፣ ፒኤችዲ (University of Warwick-UK)፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት መምህር፣ (e-mail: me2ha1@yahoo.com).

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት 50ኛ ዓመት የምሥረታ በዓሉን ሲያከብር በተዘጋጁት ተከታታይ ዓውደ ጥናቶች ውስጥ በአንዱ "በክልል ጉዳዮች የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣንና ሕጋዊ መሠረቱ" በሚል ርዕስ አጠር ባለ መንገድ የዚህ ጽሁፍ የተወሰነ ክፍል ቀርቦ ነበር፡፡ የሲምፖዚየሙ ተሳታፊዎች ያነሱዋቸው ጥያቄዎችና አስተያየቶች ግምት ውስጥ በማስገባት ለሕትመት በሚያመች አቀራረብ ተደራጅቶ የዓውደ ጥናቱ ውጤቶች ታትመዋል፡፡ አሁን ደግሞ በሂደት የተገኙ ተጨማሪ መረጃዎችና ሓሳቦች እንዲሁም የመፍትሔ አቅጣጫዎች ታክለውበት፣ እንዲሁም ተጨማሪ ክፍሎች ጭምር ታክለውና ተስፋፍቶ ቀርቧል፡፡

በጽሁፉ ረቂቅ ላይ ገንቢ ሃሳቦችና ማስተካከያዎች በመጠቆም ረገድ እገዛ ላደረጉልኝን ለሥራ ባልደረባዬ ለዶ/ር ሙራዱ አብዶ እንዲሁም ረቂቁን ለገመገሙትና ገንቢ የማስተካከያ ሐሳቦች ለጠቆሙኝ በስም ለማላውቃቸው ባለሙያዎች የከበረ ምስጋና እያቀረብኩ በጽሁፉ ውስጥ የሚንጸባረቁ ግድፈቶች ኃላፊነት ግን የእኔ ነው፡፡

መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሥርዓት ሕገ መንግሥታዊ እውቅና አግኝቶ ተግባራዊ መደረግ ከተጀመረ እነሆ ሁለት አሥርት ዓመታት ተቆጥረዋል። እንደሚታወቀው በፌዴራል ሥርዓተ መንግሥት መሠረት መንግሥታዊ ሥልጣን በፌዴራል መንግሥት ደረጃና የፌዴራሉ አባል በሆኑ መንግሥታት ደረጃ (በአገራችን አጠራር በ "ክልሎች") የሚከናወን ተግባር ነው። ከዋነኛ መንግሥታዊ ሥልጣኖች አንዱ የዳኝነት ሥራ ሲሆን ይህ መንግሥታዊ ተግባርም በሁለት ደረጃዎች ማለትም በፌዴራል እና የፌዴራል መንግሥቱ አባላት በሆኑት ክልሎች ደረጃ የሚከናወን ሆኖ ተደራጅቷል።

በርግጥ የዳኝነት ሥርዓቱ አወቃቀር ከሕግ አውጪውና ከሕግ አስፈጻሚው የፌዴራልና የክልል አደረጃጀት ለየት ያለ ቅርጽ ይንጸባረቅበታል። በሕግ አውጪው ረገድ የፌዴራል ሕግ አውጪ የሆነው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የየክልሉ ሕግ አውጪ ምክር ቤቶች ራሳቸውን ችለውና ተለያይተው የተደራጁ ናቸው። በሕግ አስፈጻሚው ዘርፍም የፌዴራሉ ሚኒስትሮች ምክር ቤትና የየክልሉ "ካቢኔዎች" የሥራ ግንኙነት እንጂ ቀጥተኛ መዋቅራዊ ትስስር የላቸውም።

የዳኝነት አካሉ ግን በፌዴራልና በክልል ደረጃ ሦስት እርከን ባላቸው የፍርድ አካላት እንደሚደራጅ ሕገ መንግሥቱ ካመለከተ በኋላ[1] ቀጥሎ ደግሞ የየክልሉ ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች እንደየቅደም ተከተላቸው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ሥልጣንና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ሥልጣን ተክተው እንዲሠሩ ሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣን እንደተሰጣቸው ተመልክቶ ይገኛል።[2] በመሆኑም የዳኝነት ሥርዓቱ አደረጃጀት ለየት ያለና በመዋቅርም ሆነ በዳኝነታዊ ሥልጣን ረገድ የመቀላቀል ባህርይ የሚታይበት ነው።

ከሕግ አውጪውና ከሕግ አስፈጻሚው በተለየ በዳኝነት ዘርፉ እንዲህ ዓይነት የተጎራረሰ አደረጃጀት የተመረጠበት ምክንያት በሕገ መንግሥት ጉባዔ ቃለ ጉባዔ የተመለከተ ሲሆን የሚከተሉት ነጥቦች በምክንያትነት ተጠቅሰዋል።[3] "እንደሌሎች አገሮች የፌዴራልና የክልል ፍርድ ቤቶች ጎን ለጎን ለማቋቋም ያልተመረጠበት ምክንያት አንደኛ ይህንኑ አደረጃጀት የሚሸከም ኢኮኖሚያዊ የበጀት አቅም ስለሌለ፣ ሁለተኛ የክልል ፍርድ ቤቶች ሥራውን ከሞላ ጎደል ሊያከናውኑት እንደሚችሉ በመታመኑ፣ ሦስተኛ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የፌዴራሉ ሕግ አውጪ የሆነው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ በክልል ውስጥ የፌዴራል ፍርድ ቤት ማቋቋም የሚችልበት አግባብ በሕገ መንግሥቱ በመደንገጉ እንደሆነ ተጠቅሷል።[4]

እንዲህ ዓይነት የዳኝነት አደረጃጀት በመፈጠሩም የክልል ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ሁለት ዓይነት የዳኝነት ሥልጣንና መዋቅራዊ ቁመና አላቸው ማለት ነው። የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክልል ፍርድ ቤትነቱ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በፌዴራል የዳኝነት ሥልጣኑ መሠረት ደግሞ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው። የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም እንዲሁ በክልሉ ጠቅላይና የበላይ ፍርድ ቤት ሆኖ በፌዴራል ሥልጣኑና ደረጃው ግን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው ማለት ነው።

ይህ ለክልል ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ድርብ ኃላፊነት የፈጠረው የተቀላቀለ አሠራር በአንድ በኩል የክልል ፍርድ ቤቶች በክልላቸው ውስጥ የፌዴራል ጉዳዮችን የፌዴራል

---

1 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት፤1987 ዓም፤ *ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ*፤ አንደኛ ዓመት፤ ቁጥር 1 አንቀጽ 78(2)(3)

2 ዝኒ ከማሁ 80(2) እና 80(4)

3 የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ጉባዔ ቃለ ጉባዔ ጥራዝ 5፤ ገጽ 31

4 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 78(2) ። በዚህ ረገድ ከጥቂት ዓመታት በፊት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይህንኑ ሕገ መንግሥታዊ ሥልጣኑን ተጠቅሞ በተወሰኑ ክልሎች ለምሳሌ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረ ሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት እንዲሁም በጋምቤላ ክልል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቋቁሞ የተወሰኑ ከብሔረሰብ ግጭት ጋር የተያያዙ የወንጀል ጉዳዮች አስተናግዶ እንደነበር ይታወሳል።

ሕግ መሠረት በማድረግ እንዲዳኙ ሥልጣን ያጎናጸፋቸው ሲሆን፣ በሌላ በኩል ግን የክልል ሕጎቻቸውን መሠረት በማድረግ ወስነው የመጨረሻ እልባት የሰጧቸው ጉዳዮች በፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ዳግም እንዲታዩ በር ከፍቷል። ይህም የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግሥቱ መሠረት የተጎናጸፉትን በክልል ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን የሚሸረሽር ክንውን ሆኖ ይታያል። በተለይም የክልል ፍርድ ቤቶች የክልል የሆነውን የሥረ-ነገር ጉዳይ በክልል ሕግ መሠረት ዳኝተው፣ በይግባኝ ብሎም በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት አስተናግደው የመጨረሻ ውሳኔ የሰጡበትንና "ጣጣውን የጨረሰ" ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር ዳግም ማስተናገዱ ከሕገ መንግሥታዊነትም አንፃር ሆነ ከአጠቃላይ የጉዳዮች ፍሰትና አመራር አንፃር ተገቢነቱ መመርመር ያለበት ነው።

በርግጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት "ማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል" ብሎ ካመነ በሰበር የማየት ከሕገ መንግሥቱ የመነጨ ሥልጣን አለኝ ብሎ ስለሚያምን[5] የሰበር ሰበሩ ክንውን ሕገ መንግሥታዊ ድርጊት ነው የሚል የጸና አቋም እንዳለው ይታወቃል። ምናልባት የሰበር ተጠሪ ሆኖ የሚቀርበው ወገን ሰበር ችሎቱን ሥልጣን የለህም የሚል ተቃውሞ ካላቀረበበት ሰበር ሰሚ ችሎቱ ምን ያድርግ? የሰበር ተጠሪው ቀርቦ በሰበር ችሎቱ ሥልጣን ላይ ጥያቄ ሳያነሳ በፍሬ ጉዳዩ ላይ መልስ መስጠት ውስጥ ከገባ የሰበሩን የመዳኘት ሥልጣን መቀበሉን ያመለክታል የሚል መከራከሪያ ሊቀርብ ይችል ይሆናል።

ሆኖም የቀረበለትን ጉዳይ ለመዳኘት ሥልጣን የለውም የሚል ተቃውሞ በተከራካሪ ወገን ባይቀርብም ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ሊያነሳው የሚገባ ነጥብ ነው። እንዲህ ስለመሆኑ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ራሱ ደጋግሞ ውሳኔ ያሳረፈበት ጉዳይ ነው።[6] የሆነ ሆኖ የሰበር ሰሚ ችሎቱ በክልል ሕግ መሠረት ተዳኝተው ያበቃላቸውን የክልል ጉዳዮች በሰበር ሰበር ያለምንም ማመንታት እያስተናገደ ይገኛል። የሰበር ሰበር በማስተናገድ ረገድ የሰበር ችሎቱ ዳኞች የልዩነት ድምጽ በሌለበት በሙሉ ድምጽ እየወሰኑ መሆኑ በእርምጃቸው ሕገ መንግሥታዊነት ላይ ሙሉ እምነት እንዳላቸው ያመለክታል።

ይህ የሰበር ችሎት በሰበር ሰበር ላይ የያዘው አቋም መከበሩ እንደተጠበቀ ሆኖ አሳማኝነቱን፣ ምክንያታዊነቱንና ሕጋዊነቱን በተመለከተ ግን አሁንም ጥያቄ ሊነሳበት፣ ውይይት ሊደረግበት፣ ትችትም ሊቀርብበት የሚቻልና የሚገባ ርዕሰ ጉዳይ ነው። የዚህ ጽሁፍ ዓላማ በዚህ ነጥብ ዙሪያ ገንቢ ውይይት እንዲደረግ ለማበረታታት ሲሆን[7] በሂደትም ሰበር ሰሚ ችሎቱ የውይይቱና የአስተያየት መንሸራሸር አካል ሆኖ አሠራሩንና አቋሙን ሊፈትሽ ይችላል የሚል ተስፋ ተሰንቋል።

የክልል ፍርድ ቤቶች የክልል ሥልጣን በሆነ ጉዳይ የክልል ሕግን መሠረት በማድረግ ዳኝነት ከሰጡና፣ በክልል ሰበርም ጭምር ጉዳዩ ታይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ፣

---

[5] በአመልካች ዘውዱ ግዛውና በተጠሪ አየለች ዘውዱ፤ (የሰበር መዝገብ ቁጥር 55273፣ ቅጽ 13) የሰበር ሰሚ ችሎቱ 'የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የክልል ጠቅላይ ጠቅላይ ፍ/ቤቶች ሰበር ችሎት በክልል ጉዳዮች ላይ የሰጡትንና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን ውሳኔ ለማረም ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ' አቋም እንደወሰደበት በፍርዶች ዝርዝር መግለጫ የተጠቀሰ ቢሆንም የፍርዱ ትንተና ውስጥ ተገብቶ ሲታይ ግን ሰበር ሰሚ ችሎቱ ይህንኑ ጭብጥ አንስቶ እንደመረመረ አያመለክትም። ዞሮ ዞሮ ግን በዚህ መዝገብ ቁጥር የተጠቀሰው ጉዳይ የክልል ጉዳይ የሆነና በክልል ሕግ መሠረት የተወሰነ እንዲሁም በክልሉ የዳኝነት አካላት በክልሉ ሰበር ችሎትም ጭምር ታይቶ ያበቃለትን ጉዳይ ተቀብሎ የመረመረ ስለሆነ በተግባሩ ይህንን መቀበሉ ስለሚያሳይ ውጤቱ ተመሳሳይ ነው።

[6] መርየሀሰን ዑመር እና መውሊድ ተክልእስማን (የሰበር መዝገብ ቁጥር 25588፤ ቅጽ 5)፤ የአዲስ አበባ ከተማ ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ዓለም ገብሩ (የሰበር መዝገብ ቁጥር 38452፤ቅጽ 8) ይመለከቷል።

[7] በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ይህ ጽሁፍ የመጀመሪያ አይደለም። በተለያዩ ጊዜያት በሕግ ትምህርት ተመራቂ ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሁፎች ነጥቡ ትኩረት አግኝቶ ምርምር የተደረገበት ሲሆን የሥራ ባልደረባዬ የሆኑት ሙራዱ አብዶም ጽሁፍ አቅርበውበታል "Review of Decision of State Courts over State Matters by the Federal Supreme Court", *Mizan Law Review,* vol. 1 no. 1 (2007) ይመለከቷል)። እነዚህ ሁሉ ጥረቶች "የቁራ ጭኸት" ሆነው እንደማይቀሩና ቀጣይ ውይይት እንደሚጋብዙ ይታመናል።

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዚሁ ጉዳይ የሰበር ዳኝነት መስጠቱ የሕገ መንግሥቱን ቃላትና መንፈስ መሠረት ያላደረገ፣ በሕግ ያልተደገፈ፣ ይልቁንም የፌዴራል ሕገ መንግሥቱ ያደራጀውን የፌዴራልና የክልሎች የዳኝነት የሥልጣን ክፍፍል አፈጻጸም አጠያያቂ የሚያደርግ መሆኑን ማሳየት የዚህ ጽሁፍ ዓላማ ነው፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎቱንም ወደማይወጣው የጉዳዮች ጫና ውስጥ ከቶ ውጤታማነቱን የሚጎዳ ድርጊት ነው ብሎ የሚከራከር ፍሬ ሓሳብ ጽሁፉ ይዟል፡፡ የጽሁፉ ማጠቃለያም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በክልሎች የመዳኘት ሉዓላዊ ሥልጣን ውስጥ እንዳይገባ ይጠይቃል፡፡

ጽሁፉ በስምንት ዋና ክፍሎች ተከፋፍሎ የሚቀርብ ሲሆን፣ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ክፍሎች በኢትዮጵያ የሰበር ሥርዓትን ታሪካዊ አመጣጥ እንዲሁም የፈረንሳይን ሰበር ሥርዓት አጀማመርና በሂደት ሥርዓቱ ያደረገውን ለውጥ በአጭሩ ይዘግባሉ፡፡ በመቀጠልም አሁን ያለው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አሠራርና የጉዳዮች ፍሰት ፍኖተ ካርታ (roadmap) እንዲሁም ይህ የጉዳዮች ፍሰት የፈጠራቸው ተግዳሮቶች በሦስተኛውና በአራተኛው ክፍሎች ተዳሰዋል፡፡ ከዚያ ቀጥሎ የሰበር ሰሚ ችሎቱ ይህንኑ አሠራር እንዲከተል ያስገደዱት በዋና ምክንያትነት የሚጠቀሱ የሕግና የፍሬ ነገር ነጥቦች በአምስተኛው ክፍል ቀርበው፣ እነዚህ ምክንያቶች ምን ያህል ሕጋዊና አሳማኝ እንደሆኑ በጽሁፉ ስድስተኛ፣ ሰባተኛና ስምንተኛ ክፍሎች ይገመገማሉ፡፡ በመጨረሻም በጽሁፉ ማጠቃለያ የመፍትሄ አማራጮች ቀርበዋል፡፡

1. የሰበር ሥርዓት ታሪካዊ አመጣጥ በኢትዮጵያ

"ሰበር" የሚለው ቃል በአማርኛ መዝገበ ቃላት ትርጉም የተሰጠበት ሲሆን መስበር፣ መሰባበር፣ መቀጥቀጥ፣ ማንከት፣ ማድቀቅ ከሚሉ ቃላት ጋር ተያይዞ የተተረጎመ መሆኑን እንገነዘባን፡፡[8] ቃሉ casser ከሚል ግሥ መንጭቶ cassation ከሚል ስርወ የፈረንሳይ ቃል እንደተወሰደ የሚታመን ሲሆን በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ጥቅም ላይ መዋል የጀመረው በ1900 በፈረንሳይና ኢትዮጵያ መካከል በተፈረመው የንግድና የወዳጅነት ውልና ውሉን ተከትሎ በወጣው የሥነ ሥርዓት ደንብ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡[9] ከውሉ በመነጨ ጉዳይ አለመግባባት ቢፈጠር ተቀብሎ የሚመረምር የቆንስል ፍርድ ቤት ውሉ ያቋቋመ ሲሆን፣ በዳኞቹ መካከል መለያየት ቢፈጠር ጉዳዩ ለንጉሠ ነገሥቱ ችሎት ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለማስቻል ያለመ ነበር፡፡[10] በወቅቱ የንጉሠ ነገሥቱ ችሎት የሰበርን ሥራ ማከናወኑ ነበር፡፡ ነገር ግን የሰበሩ የተፈጻሚነት ወሰን በዳኞቹ መካከል መለያየት ሲኖር የሚመጣ የመጨረሻ መፍትሔ እንጂ ዳኞቹ በሙሉ ድምጽ በሰጡት ውሳኔ ላይ የሚያገለግል አልነበረም ማለት ነው፡፡

የሰበር ሥርዓት በሌሎች አገራትም እንደሚሠራበት መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ እንደ ፈረንሳይ ባሉ አገሮች (በሚቀጥለው ክፍል እንደተገለጸው) የመጠሪያው ትርጉም እየሰፋ መሄዱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሰበር ችሎቶች በመደበኛው የሰበር ተግባራቸው አቤቱታ የቀረበበትን የመጨረሻ ውሳኔ ሰብረው መጀመሪያውኑ ውሳኔውን ወደሰጠው የበታች ፍርድ ቤት ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላለ ሌላ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሰጥበት ይልኩለታል እንጂ በጉዳዩ ላይ የራሳቸው ውሳኔ አይሰጡበትም ነበር፡፡ በሌሎች አገሮች ደግሞ ሰበር ችሎቶች ቀዳሚውን ውሳኔ በመስበር ላይ ብቻ ሳይወሰኑ የተሰበረውን ውሳኔ የሚተካ የራሳቸው ውሳኔ ሊያሳርፉበት ሥልጣን አላቸው፡፡[11]

---

[8] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (1948 ዓ.ም.)፤ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ መዝገበ ቃላት* ገጽ 847

[9] ታምሩ ወንድማገኘሁ "ፍትሕ ወርትዕ"፤ *ሕጋዊነት* ቅጽ 3፤ ቁጥር 5 (ነሐሴ 1983 ዓ.ም.) ገጽ 78

[10] ዝኒ ከማሁ፤

[11] በዚህ ነጥብ ዙሪያ ሰፋ ያለ ሃሳብ ለማግኘት፤ ቢልልኝ ማንደፍሮ "የሰበር ሥርዓት በኢትዮጵያ" *ሕጋዊነት*፤ ቅጽ 1፤ ቁጥር 1፤ (ሚያዝያ 1981 ዓ.ም.) ገጽ 37-53 ይመልከቱ

በአገራችን በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የሰበር ሥርዓት "በዙፋን ችሎት" ውስጥ የንጉሡን የፍትሕ ምንጭነት በሚያሳይ መንገድ ተደራጅቶ ነበር። አሠራሩም "ፍርድን ስለማጣራት" በሚለው የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ምዕራፍ ሥር (ከቁጥር 361-370) የሚሸፈን ነበር። "ንጉሡ የፍትሕ ምንጭ ናቸው" የሚል አስተሳሰብ ሥር የሰደደበት ወቅት ስለነበር የይግባኝ መብቱን አሟጦ የተጠቀመ ባለጉዳይ ነገሩ ከፍትሕና ርትዕ አንፃር እንዲታይለት ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት [ለዙፋን ችሎት] አቤቱታ የማቅረብ መብት ነበረው።[12] የዙፋን ችሎቱ በአንዳንድ አገሮች እንደሚደረገው አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ በመስበር ላይ ብቻ ሳይወሰን በጉዳዩ ላይ የራሱን ውሳኔ ወይም ትእዛዝ የመስጠት ሥልጣንም የተጎናፀፈ ነበር።[13] የዙፋን ችሎቱ አሠራር የሰበር ፅንሰ ሓሳብ መጣበት ከተባለው ከፈረንሳይ የሰበር አሠራር ጋር የሚጣጣም አልነበረም።

በደርግ ዘመን ከንጉሠ ነገሥቱ መነሳት ጋር የዙፋን ችሎት ፈርሶ የዳኝነት ማጠናቀቂያ ሂደት የይግባኝ ውሳኔ ሆኖ ለአሥራ አምስት ዓመታት ያህል ከዘለቀ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ-መንግሥት በ1980 ዓ.ም. ሲታወጅ የሰበር ፅንሰ ሃሳብ የዳኝነት ሥርዓቱ አካል ሆኖ እንደገና ወደ ሕግ ሥርዓታችን ተመልሶ መጣ። ሕገ-መንግሥቱን ተከትሎ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 9/1980፣ አንቀጽ 4(4) ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሰጣቸው የዳኝነት ሥልጣኖች አንዱ "በጠቅላይ ፍርድ ቤት ወይም በሌሎች ፍርድ ቤቶች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ሲገኝ ወይም በሥነ ሥርዓት ሕጎች ውስጥ በተመለከቱት ሌሎች ምክንያቶች በሰበር መስማት"[14] ነው። ይህ አዋጅ የሰበር ሥርዓት መኖሩን አስረግጦ ካስቀመጠ በኋላ በአንቀጽ 5(1) ሥር ደግሞ "… የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር የሚሰማው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሲፈቅድ ወይም ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ተቃውሞ ሲያቀርብ" እንደሆነ ተመልክቷል።[15]

በርግጥ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ-መንግሥት በሥራ ላይ የቆየው ከሦስት ዓመታት ላልበለጠ ጊዜ ስለነበር ስለውጤታማነቱ ስፋ ያለ መረጃ ማግኘት አይቻልም። ነገር ግን የድንጋጌው አቀራረፅ የሰበር ጉዳይ የፍርድ ቤቶች ጉዳይ ብቻ ሳይሆን "ሶሻሊስት ሕጋዊነት"ን የመከታተል ኃላፊነት ተሰጥቶት የነበረውን ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግም እንደሚመለከት ይጠቁማል። የሆነ ሆኖ የመጨረሻ ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ሲገኝ በሰበር እንዲመረመር የማድረግ መርህ "ዘመን ተሻጋሪ" ሆኖ እስከ አሁንም ድረስ የዳኝነት ሥርዓታችን አካል ሆኖ እየተሠራበት ይገኛል። እንዲያውም አሁን ባለው የሰበር አሠራር የሰበር ሰሚ ችሎቱ የቀረበለትን ጉዳይ ለመፍታት ሲል የሚሰጠው የሕግ ትርጉም በያዘው መዝገብ ላይ ሳይወሰን ለሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች የአስገዳጅነት ኃይል እንዳለው ተደንግጎ ይገኛል።[16]

ስለዚህ በንጉሡ ዘመን የኢትዮጵያ ሰበር ሥርዓት በአስፈጻሚው ማለትም በዙፋን ችሎት በኩል የሚከናወንና ፍትሕና ርትዕን መሠረት በማድረግ የሚመዘን ነበር፤ ከደርጉ የመጨረሻዎቹ የሥልጣን ዘመናት ወዲህ ደግሞ የዳኝነት አካሉ ዘርፍ ሆኖ መሠረታዊ የሕግ ስህተትን ለማረም ያለመ ድርጊት ሆኖ ቀጥሏል። በሦስቱም ሥርዓቶች ግን የኢትዮጵያ የሰበር ሥርዓት (ስሙ እንደሚያመለክተው) ቅሬታ የተነሳበትን የበታች የዳኝነት አካል ውሳኔ በመስበር ላይ ሳይወሰን የራሱን ውሳኔ በመስጠት የተሰበረውን ውሳኔ የሚተካና ክፍተቱን የሚደፍን ዳኝነታዊ ክንውን ነው።

---

12 የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 322

13 ዝኒ ከማሁ ቁጥር 370

14 አንቀጽ 4(4)፤የጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 9/1980፤ *ነጋሪት ጋዜጣ፤* ቁ.9፤ መስከረም 6/1980 ዓ.ም.

15 ዝኒ ከማሁ

16 አዋጅ ቁጥር 454/1997

2. የፈረንሳይ ሰበር ሥርዓት አጭር ምልከታ

ሰበር የይግባኝ ሥርዓት እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡ ምክንያቱም ይግባኝ በአንድ ዳኝነት ላይ የሚቀርብ የፍሬ ጉዳይና የሕግ ነጥብ ቅሬታን የሚመለከት ክርክር ሲሆን የሰበር ክርክር የሚካሄደው በመጨረሻው የዳኝነት እርከን በተሰጠ ዳኝነት[17] ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት[18] መፈፀሙን በማሳየት በሚቀርብ አቤቱታ[19] መነሻ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል የአውሮፓ ፍርድ ቤት (European Court of Justice) የአውሮፓን ኅብረት ሕግ አተረጓጎም በሚመለከት ትርጉም የመስጠት ሥልጣን ያለው እንደመሆኑ ይህ ሥልጣን ከሰበር ጋር እንደሚመሳሰል ይነገራል፡፡ ይህ ምሳሌ የተነሳው አውሮፓ አንድ አገር ናት ለማለት ሳይሆን መሠረታዊ የሕግ ትርጉምን የማረም ተግባር ከአገርም አልፎ አህጉራዊ ኅብረትንም ጭምር የሚመለከት መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከአሀዳዊ አገሮች በቀር የፖለቲካው ትስስር ፌዴራላዊ፣ ኮንፌዴራላዊ፣ አህጉራዊ ወዘተ … እየሆነ በሄደ መጠን መሠረታዊ የሕግ አተረጓጎም ስህተት በዳኝነቱ የመጨረሻ አካል ሲደረግ የሰበር ችሎት የሚመለከታቸው ጉዳዮች ውሱን ናቸው፡፡

በአንፃሩ ደግሞ በአሃዳዊ ሥርዓቶች የሚገኙ የሰበር ሥርዓቶች መሠረታዊ የሕግ ስህተትን ለማረም የሚሰጡት ውሳኔ በሕጎቹ ወይም በጉዳዮቹ ዓይነት የተገደበ አይደለም፡፡ የሰበር ሥርዓት የተጀመረው በፈረንሳይ መሆኑ፣ እንዲሁም ወደሌሎች አገሮች ጭምር ተግባራዊ መሆኑና መስፋፋቱ ይነገራል፡፡[20] ከፈረንሳይ አብዮት ግቦች መካከል አንዱ የሕግ ወጥነትን በፈረንሳይ ማስፈን ስለነበርና በአተረጓጎም ረገድ በፍርድ ቤቶች መካከል መናበብና ተጓዳኝነት እንዲኖር ስለተፈለገ አንድ ወጥነት ያላቸውን ሕጎች በመተርጎም ሂደት ስህተት ሲፈጠር ይህን ስህተት የሚያርም (የሚሰብር[21]) ሥርዓት ተዘረጋ፡፡

የፈረንሳይ ሰበር ሰሚ ተቋም የተመሠረተው እ.ኤ.አ. በ1790 ነበር፡፡[22] በፈረንሳይ የሰበር ሥርዓት ሲጀመር *Tribunal de Cassation* (የሰበር ሰሚ ችሎት) በሚል መጠሪያ ተዋቅሮ የፍርድ ቤት ሳይሆን የሕግ አውጭው አካል ነበር፡፡ ሥልጣኑም የተገደበ ስለነበር ቅሬታ የቀረበበትን የሕግ ትርጉም በሚመለከት የሕግ ስህተት ያለውን ውሳኔ ውድቅ ከማድረግ ባሻገር የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠውን ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር ውሳኔ መቀበል ነበረበት፣ ውድቅ የተደረገውን የሕግ ትርጉም በሚመለከትም ውሳኔ በሰጠው ፍርድ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ የመላክ (renvoi) እንጂ ሌላ አስገዳጅ ትርጉም የመስጠት ሥልጣን አልነበረውም፡፡[23] በ19ኛው ክፍለዘመን፣ ችሎቱ ከሕግ አውጭው የመንግሥት አካል ወጥቶ በሕግ ተርጓሚው ዘርፍ ሥር እንዲደራጅ ተደረገ፡፡ ከሕግ አውጭው ተለይቶ በችሎትነት ሲቋቋም መጠሪያውም የሰበር ሰሚ ፍርድ ቤት ተሰኘ፡፡[24]

---

[17] በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 22(4) "የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበትን (final decision protested)" የሚለውን ሐረግ ይመለከቷል፡፡

[18] በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 22(2)ን ይመለከቷል፡፡

[19] በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 22(2) "…ጉዳዩ በሰበር እንዲታይለት የሚፈልግ አቤቱታ አቅራቢ…" የሚለውም ሐረግ የሚያመለክተው የሰበር አቤቱታ ከይግባኝ ያለውን ልዩነት ነው፡፡ የዚሁ ሐረግ አንቀጽ የእንግሊዝኛ ቅጂ የተጠቀመው "The applicant for a hearing in cassation" የሚል ነው፡፡

[20] S. Pompe (2005), *The Indonesian Supreme Court: A Study of Institutional Collapse*, SEAP Publications, ገጽ 216

[21] በፈረንሳይኛ "casser"" የሚለው ቃል በእንግሊዝኛ "to break to quash" በአማርኛ ደግም መስበር፣ ማለት ነው፡፡

[22] ችሎቱ የተመሠረተው ከፈረንሳይ የእኤአ 1789 አብዮት አንድ ዓመት በኋላ ሲሆን፤ የወቅቱ የፍትሕ ሥርዓት ለውጥ አካል ነበር፡፡

[23] Pompe፤ ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 20 የተጠቀሰ፣ ገጽ 217

[24] *Cour de cassation*

ምንም እንኳ ወጥ የሆኑ ስብስበ-ሕግጋት[25] በፈረንሳይ መውጣታቸው በርካታ አዎንታዊ ሚና የነበራቸው ቢሆንም፣ ሕጎች ሲወጡ ሕግ አውጭው ባልተገነዘባቸው አዳዲስ ኩነቶችና ነባራዊ ለውጦች ምክንያት ሕጉ እስኪሻሻል ድረስ የሕግ አተረጓጎም መዘበራረቅ መከሰቱ ስለማይቀር፤ የሕግ ተርጓሚው በዚህ ረገድ ሊያደርግ የሚችለውን አስተዋጽኦ በሂደት መገንዘብ ተቻለ። ስለሆነም እ.ኤ.አ. በ1837 የፈረንሳይ ሰበር ሰሚ ፍርድ ቤት በሚቀበላቸው አቤቱታዎች መነሻ የሕግ ትርጉም ስህተት መደረጉን መሠረት በማድረግ የመጨረሻውን ዳኝነት ውድቅ በማድረግ እርማት እንዲደረግ ጉዳዩን ወደፍርድ ቤት ከመመለስ (renvoi) ባሻገር ሰበር ሰሚው ችሎት ራሱ የሕግ ትርጉም ሰጥቶ ለጉዳዩ እልባት እንዲሰጥ[26] ሥልጣን ተሰጠው።

ከዚህም በተጨማሪ በጊዜ ሂደት የሰበር ሰሚው ፍርድ ቤተ ሥልጣን እየሰፋ መጥቶ በአሁኑ ወቅት ከስሙ በቀር ችሎቹ ወደ መጨረሻው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትነት (court of last resort) ተለውጧል ማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ ይኸው ፍርድ ቤት በይግባኝና በሰበር ደረጃ በሚያያቸው ጉዳዮች ረገድ ያለው የዳኝነት ሥልጣን አድማስ (scope of jurisdiction) ይለያያል። በዚህ ረገድ በእንግሊዝና አሜሪካ የሕግ ሥርዓቶች ጠንካራ የይግባኝ ሥርዓት እንዳለ ገልጸው፣ የፈረንሳይ የሰበር ሥርዓት ግን መሠረታዊ የሕግ ስህተትን በማረም ብቻ የሚያተኩር ሥርዓት መሆኑን የተቹ ጸሀፊዎች[27] ቢኖሩም ይህ ትችት የይግባኝንና የሰበርን ሥርዓቶች አላግባብ ከማመሳሰል የመነጭ ይመስላል። እንደዚያም ሆኖ፣ የፈረንሳይ ሰበር ፍርድ ቤት (ስሙን ይዞ ከመቀጠሉ በቀር) ሥልጣኑ እየሰፋ በመሄዱ የወቅታዊው ተግባሩ ሁለንተናዊ አድማስ (overall scope) ከይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ጋር የሚመሳሰል ሆኗል።[28]

ስለሆነም የፈረንሳይ ሰበር ፍርድ ቤት በአሁኑ ወቅት ካለው ተግባርና ሥልጣን አኳያ ከኢትዮጵያ የሰበር ሥርዓት ጋር አይመሳሰልም። አሃዳዊ የፖለቲካ ሥርዓት ያላት ፈረንሳይ ፌዴራላዊ ሥርዓት ካላት ኢትዮጵያ ትለያለች። ከዚህም በተጨማሪ የፈረንሳይ ሰበር ፍርድ ቤት በአሁኑ ወቅት የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትን ተግባራትን ጭምር የሚያከናውን እንደመሆኑ ፍርድ ቤቱ እንደ ሰበር ሰሚ ችሎት ብቻ የሚታይ አይደለም።

3. ወደ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የሚቀርቡ ጉዳዮች ፍሰት (case flow)

በአሁኑ ወቅት ያለውን የፍርድ ቤት ጉዳዮች ፍሰት "ሁሉም የሙግት መንገዶች ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያመራሉ" ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።[29] ከፌዴራል መጀመሪያ ፍርድ ቤት የተነሳ ጉዳይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኩል ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ብሎም ወደ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚያመራበት ሂደት አለ። ይህ ቀጥተኛው የፌዴራል አውራ ጎዳና ነው። ነገር ግን ብቸኛው የሰበር መዳረሻ መንገድ አይደለም። እንዲያውም ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት የሰበር ሰሚ ችሎቱ መዛግብት በዚሁ የፌዴራል አውራ ጎዳና የሚገቡ አይደሉም።[30]

የክልል ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግሥቱ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት የሚያስተናግዱዋቸው የፌዴራል ጉዳዮች አሉ። እነዚህ ጉዳዮች እንደየጉዳዩ ሁኔታ ከክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም

[25] "Code" የሚለው ቃል በርካታ የሕግ ዘርፎችን በአንድነት አጠቃሎ የያዘ እንደመሆኑ ሕግ ከሚለው የሰፋ ቃል ሊፈለግለት ይገባል።

[26] "… impose a l' interprétation de la loi."

[27] ለምሳሌ H. Merryman (1985), *The Civil Law Tradition* (Stanford University Press), p. 39 cited by Pompe, supra note 20.

[28] Pompe ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 20 የተጠቀሰ፣ ገጽ 217

[29] የሙያ ባልደረባዬ የሆኑት አቶ ዮሴፍ አእምሮ ለአንድ ዓውደ ጥናት ባቀረቡት የመወያያ ጽሁፍ ሥር ጉዳዮች ከአሥራ ስድስት የመዳኘት ሥልጣን የተሰጣቸው ተቋሞች መንጭተው ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት እንደሚደርሱ የሚያሳይ የጉዳዮች ፍሰት ሠንጠረዥ አቅርበው ነበር። ሌላ አንድ ተጨማሪ መስመር በዓውደ ጥናቱ ውይይት ሂደት ታክሎ በአጠቃላይ የፍሰት መስመሮቹ ብዛት አስራ ሰባት ደርሷል።

[30] ይህ ፍሬ ነገር በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ረዘም ላለ ጊዜ በዳኝነት ሥራ ካገለገሉ አንዳንድ ዳኞች ጋር ካደረግኩት ውይይት የተገነዘብኩት ጉዳይ ነው።.

ከክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይጀምሩና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በኩል ወይም ወደዚያ መሄድ ሳይጠበቅባቸው ወደ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚቀርቡ ናቸው፡፡[31] በሌላም በኩል ርዕሰ ጉዳዮቹ የክልል ጉዳይ ሆነው እያሉ፣ የተመረመሩትም በክልል ፍርድ ቤት በክልላዊ ፍርድ ቤትነቱ መሆኑ እየታወቀ፣ ጥቅም ላይ የዋለው ሕግም የክልል ሕግ ሆኖ እያለ፣ "የመጨረሻ ውሳኔ" ናቸው እየተባለ በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ታይተው የተወሰኑም ጭምር ወደ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ይቀርባሉ፣ ይመረመራሉ፣ ይጸናሉ፣ ይሻራሉ፣ ተሻሽለው ይወሰናሉ ወይም ከመመሪያ ጋር ወደታች ይመለሳሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች፣ በከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች፤በወታደራዊ ፍርድ ቤቶች፤ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርዶች፤ በግብር ይግባኝ ጉባኤዎች፤ በአስተዳደር ፍርድ ቤቶች እና በማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች የተከፈቱ ፋይሎች በፌዴራል ወይም በክልል ፍርድ ቤቶች በኩል ወይም በቀጥታ ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያመራሉ፡፡ ሌላው ቀርቶ ከማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ጉባኤ፣ ከፕራይቬታይዜሽን ቦርድ የተነሱና ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ያልቀረቡም ጉዳዮች ቢሆኑ "የመጨረሻ ውሳኔ" ናቸው እየተባለ በሰበር ሰሚ ችሎቱ እየተመረመሩ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ በተለይ በፍርድ ቤት በይግባኝ ወይም በሌላ መንገድ ሳይመረመሩ ከአስተዳደር መሥሪያ ቤቶች በቀጥታ ወደ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርበው የመስተናገዳቸው ሕጋዊነት በእጅጉ የሚያወያይ ጉዳይ ነው፡፡

የድርጊቱን ሕጋዊነት ለማሳየት እየቀረበ ያለው መከራከሪያ ውሳኔዎቹ የመጨረሻ እስከሆኑ ድረስ ከፍርድ ቤት ደጃፍ ባይደርሱም በሰበር የሚስተናገዱ ናቸው የሚል ነው፡፡[32] ሆኖም በዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ግንዛቤ ሕገ መንግሥቱ "ማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ" ሲል የፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ማለቱ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህንኑ ሐረግ የያዘው የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80(3)(ሀ) "የፍርድ ቤቶች ጣምራነትና ሥልጣን" በሚል አንቀጽ ሥር "ስለፍርድ ቤቶች አወቃቀርና ሥልጣን" በሚደነግገው የሕገ መንግሥቱ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ በመሆኑም አንቀጹም ሆነ ምዕራፉ የሚያወሱት ስለ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔ እንጂ ስለማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ አይደለም፡፡

ሰበር ልዩ ሥርዓት ስለሆነ በጠባቡ መተርጎም ያለበት ነው፡፡ ለሕገ መንግሥቱ ቃላትና ሐረጎች የሕገ መንግሥቱ አውጪዎች ካሰቡት ውጭ ትርጉም ሊሰጣቸው አይገባም፡፡ ከዚህም አልፎ "ማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ" የሚለው በሰፊው ከተተረጎመ ሰበር ችሎቱ ሊወጣው ወደማይችል የጉዳዮች ጎርፍ ውስጥ የሚከተው እንዳይሆን ሥጋት አለ፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በየሥልጣን ዘርፉ የሚያሳልፋቸው በርካታ የመጨረሻ ውሳኔዎች ያጋጥማሉ፡፡ ይህ ርዕሰ ጉዳይ ራሱን የቻለ ጥልቅ ምርምር ሊደረግበት ስለሚገባና በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በስፋት የሚዳሰስ ባለመሆኑ፣ ሌሎች ባለሙያዎች በጭብጡ ላይ ይጽፋሉ ተብሎ ይገመታል፡፡[33]

[31] ለምሳሌ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግ መሠረት በማድረግ የሚቀርቡ የግልም ሆነ የወል የሥራ ክርክሮች ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ነው በቀጥታ ወደ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚቀርቡት፡፡

[32] አቶ ዮሐንስ ኅሩይ "ስለሰበር ሥልጣንና ስለ ሥርዓቱ ጥቂት ማስታወሻዎች" በሚል ርዕስ *በኢትዮጵያ ጠበቆች የሕግ መጽሔት* ቅጽ 3፤ ቁጥር 1 (መጋቢት 2001 ዓ.ም.) ባሳተሙት ጽሁፍ ማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ ከፍርድ ቤት የመነጨ ባይሆንም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ካለበት በሰበር መመርመሩ ተገቢ ነው የሚል አቋም አንጸባርቀዋል፡፡

[33] በዚህ ረገድ በቅርቡ ብርሃኑ በየነ የተባሉ ጸሐፊ "Cassation Review of Arbitral Awards: Does the Law Authorize It?" በሚል ርእስ በ*Oromia Law Journal*, Vol. 2, No.2 (2013) pp.112-137 ውይይት የሚጋብዝ ሃሳባቸውን አካፍለዋል፡፡

4. ከፒራሚድ ይልቅ በዋርካ የሚመሰሉ የጉዳይ ፍሰቶች ምንጭና ተግዳሮቶች

እንደሚታወቀው መደበኛውና ተለምዷዊው የጉዳዮች ፍሰት (case flow) የግብጽ ፒራሚድ ዓይነት ቅርጽ ይንፀባረቅበታል፡፡ ማለትም ከታች ሰፋ ብሎ ይጀምርና ወደ ላይ እየወጣ ሲሄድ የጉዳዮች ቁጥር እየቀነሰ ስለሚሄድ የላይኛው ጫፉ እየጠበበ ይሄዳል፡፡ ስለሆነም ወደ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚደርሱ ጉዳዮች ቁጥራቸው በእጅጉ የተመጠነ ነው፡፡ የሰው ኃይል አደረጃጀቱም የዚሁ ነፀብራቅ ነው፣ ማለትም የዳኞች ቁጥርም በበታች ፍርድ ቤቶች በዛ ብሎ ወደ ላይ እየተወጣ ሲኬድ ቁጥራቸው እያነሰ፣ ብቃትና ጥራታቸው ግን እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ይህን የመሰለ ጤናማ የጉዳይ ፍሰትና የሰው ኃይል አደረጃጀት ሲኖር የሰበር ሰሚ ችሎቱ ለጥቂት ጉዳዮች በቂ ጊዜና ተገቢ ሙያዊ ትኩረት ሰጥቶ በጥልቀትና በብቃት በመመርመር አስገዳጅ ብቻ ሳይሆን አሳማኝ ውሳኔም እንዲሰጥባቸው ዕድል ያገኛል፡፡ በዚህ ረገድ በአጠቃላይ የፍትሕ ሥርዓቱ ጭምር የአሠራር ቀልጣፋነትና ውጤታማነት፣ እንዲሁም የይዘት ተገማችነትና ተደማጭነት እንዲኖረው የሰበር ሥርዓቱ የበኩሉን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡

በአንፃሩ ግን፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የጉዳዮች ወቅታዊ ፍሰት የፒራሚድነት ሳይሆን የዋርካነት ቅርጽ የሚንፀባረቅበት ሆኗል፡፡ ከታች ሰብሰብ ብሎ ጭንቅላቱ ላይ የሰፋ ቅርፅ ፈጥሯል፡፡ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት ካለው የመዝገቦች ብዛት የሚልቅ መዝገብ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ዘንድ ተከማችቶ እንደሚገኝ በተለያዩ መድረኮች ሲገለጽ ይደመጣል፡፡ ለምሳሌ በሰኔ ወር 2007 ዓ.ም. በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት 3578 በክርክር ላይ ያሉ መዝገቦች የተመዘገቡ ሲሆን ስርጭታቸው የሚከተለውን ይመስላል፡፡ በይግባኝ ደረጃ 684 ማለትም 299 መዝገቦች በፍትሐ ብሔር ችሎት ፊት 385 መዝገቦች ደግሞ በወንጀል ችሎቶች እጅ እንዳሉ ያመለክታል፡፡ በአንፃሩ የሰበር ችሎቱ መዛግብት ሲታዩ 2894 ሆነው 1238 መዝገቦች በሰበር ሰሚ ችሎት ፊት የተቀሩት 1656 መዝገቦች ደግሞ በአጣሪ ሰበር ችሎቶች እጅ እንዳሉ መረጃው ያመለክታል፡፡[34] ማለትም፣ በሰበር ሰሚ ችሎቱ እጅ ያለው የመዝገብ ብዛት በይግባኝ ሰሚ ችሎቶቹ እጅ ካለው መዝገብ ከአራት እጥፍ በላይ ነው፡፡

ለዚህም ምክንያቱ እላይ በተገለጸው ፍኖተ ካርታ መሠረት ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎት በይግባኝ መልክ ሳይቀርቡ በቀጥታ ወደ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚቀርቡ ጉዳዮች ስላሉ ጭምር ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ሰበር ሰሚ ከሰው ኃይል አደረጃጀቱ ጋር ያልተመጣጠነ የጉዳዮች መጨናነቅ ይታይበታል፡፡[35] እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም የሰበር ሰሚ ችሎቱ ለእያንዳንዱ ጉዳይ የሚመድበው ጊዜና የትኩረት መጠን ማነሱ ስለማይቀር ውሳኔው አልፎ አልፎ በበቂ ምክንያትና ትንተና ያለመደገፍ ችግር ያጋጥመዋል፡፡ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠው ውሳኔ ተመሳሳይ ጭብጥ ኖሯቸው በፍሬ ነገርም ረገድ ተመሳሳይነት ባላቸው ጉዳዮች አስገዳጅ የሕግ አተረጓጎም የሚያስከትል መሆኑ የማይቀር ቢሆንም የማሳመን ብቃቱ ግን በሂደት ሊሸረሸር ይችላል የሚል ስጋት አለ፡፡ ለሰበር ውሳኔ ዘላቂ ተቀባይነት መሠረት ሊሆን የሚገባው ደግሞ አሳማኝነቱ እንጂ አስገዳጅነቱ አይደለም፡፡ ምክንያቱም አስገዳጅነቱን ከሕግ ስለተጎናጸፈው "አረረም መረረም" አስገዳጅ መሆኑ አይቀርም፡፡

ምንም እንኳ ጉዳዩ ጠለቅ ያለ ጥናት የሚጠይቅ ቢሆንም በዚህ ጸሐፊ አስተያየት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም እንዲሰጥ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው (1997 ዓ.ም.) ጀምሮ ባለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ "ይበል" የሚያሰኙ ወሳኝ ፍርዶች (landmark decisions) አስተላልፎ ለሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች የትርጉም መሠረት ሆነው በማገልገል ላይ ናቸው፡፡ የውሳኔዎቹ ችግር ፈቺነት አንድ ነገር ሆኖ ውሳኔዎቹ ለበታች ፍርድ ቤቶችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች ተደራሽ ይሆኑ ዘንድ በወረቀት የታተመና (hard copy)

---

[34] ሰኔ 4 ቀን 2007 ዓ.ም. ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረ ገጽ የታተመ መረጃ፡፡

[35] ለሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚቀርቡት ጉዳዮች ከግዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመሩ በመምጣታቸው በቅርቡ (2007 ዓ.ም.) ሰበር ሰሚ ችሎቱ አንድ ችሎት ብቻ መሆኑ ቀርቶ በሁለት ችሎት እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡ ይህ ደግሞ የራሱን ችግር ይዞ መምጣቱ አይቀርም፡፡ ለምሳሌ በተመሳሳይ ጉዳይ ሁለቱ ችሎቶች የተለያየ የሕግ አተረጓጎም ቢከተሉ ለበታች ፍርድ ቤቶች አስገዳጅ የሚሆነው ትርጉም የትኛው ሊሆን ነው?

በኤሌክትሮኒክ (soft copy) ቅጂም አደራጅቶ ማቅረቡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱን በእጅጉ የሚያስመሰግነው ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት የሚሰጠው የሕግ ትርጉም ለተያዘው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ተመሳሳይ ጭብጥና ፍሬነገር ባላቸው ጉዳዮች ላይ ጭምር አስገዳጅ እንዲሆን በሕግ የደነገገውን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ማመስገን ተገቢ ነው፡፡

ከውሳኔ ጥራት አንፃር የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ በቅርበት በሚከታተለው የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግ ዙሪያ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ያስተላለፋቸው ውሳኔዎች በአንድ በኩል አሠሪ በአሠሪነቱ ሊኖረው ለሚገባ መብት ተገቢ እውቅና የሰጡ ብሎም ኢንቨስትመንትን የሚያበረታቱ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሠራተኛውን መሠረታዊ መብቶች የሚያስጠብቁ የሕግ አተረጓጎም ዘይቤዎችን የተከተሉና ሚዛን የጠበቁ ናቸው፡፡ ሕግ በልማት ላይ (law in development) ሊኖረው የሚገባውን ገንቢ አስተጽኦ የሚያጎለብቱ ናቸው ማለትም ይቻላል፡፡[36] ይህ ሲባል ግን በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ ዙሪያ በሰበር ሰሚ ችሎቱ የተሰጡት የሕግ ትርጉሞች ከትችት የጸዱ[37] ነበሩ ማለት ባይቻልም፣ ከሞላ ጎደል የአሠሪና ሠራተኛን ተገቢ ጥቅም (legitimate interest) ሚዛን በጠበቀ ሁኔታ ሕጉ እየተተረጎመ ስለመሆኑ አፍ ሞልቶ መመስከር ይቻላል፡፡

ሰበር ሰሚ ችሎቱ በጉዳዮች ብዛት እንዲጨናነቅና እንዲጥለቀለቅ ከተደረገ ግን እነዚህን ከመሰሉ አገራዊ ፋይዳ ካላቸው የኢንቨስትመንትና የኢኮኖሚ ጉዳዮች ወጥቶ ከማኅበራዊ ፍርድ ቤት ተነስተው በወረዳ ፍርድ ቤት በይግባኝ ታይተው "የመጨረሻ ውሳኔ" የተባሉና በክልል የሰበር ሥርዓት ተስተናግደው ያበቃላቸው ጥቃቅን ጉዳዮች በመመርመር ተጠምዶ ይቀራል ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በምንም ዓይነት መመዘኛ ለአገርም ሆነ ለሕዝብ እንዲሁም ለተከራካሪ ወገኖች የሚበጅ አይደለም፡፡

የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ክልላዊ ፋይዳ ያላቸውንና በክልል ሕግ መሠረት ታይተው የተቋጩ ጉዳዮችን ጭምር እያስቀረበ እንደሚያከራክር ሲታወቅ በክልሉ የመጨረሻው የዳኝነት አካል በተሰጠ ውሳኔ ያልረኩ ወገኖች አዲስ አበባ ደርሰው ጉዳያቸውን በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት አስመርምረው "ቁርጡን እስካላወቁ" ልባቸው ላይረካ ይችላል፡፡ የኅብረተሰባችን የተሚጋችነትና የእልህ ስሜት በቀላሉ የሚታይ እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በተለይም በታሪክ አጋጣሚ ባለፉት መንግሥታዊ ሥርዓቶቻችን መናገሻ ከተማችን አዲስ አበባ ለዘመናት የፍትሕ ምንጭ ናት ተብላ ትታመን ስለነበር ተቀማጭነቱን አዲስ አበባ ያደረገውና ተዘዋዋሪ ችሎት እንኳን ያላደራጀው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሁሉንም ጉዳዮች እያስቀረበ መዳኘነቱ የጥንቱን የአዲስ አበባ የፍትሕ ምንጭነት ሥነ-ልቦና መልሶ እንዲያቆጠቁጥ በር የሚከፍት እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡

በርግጥ የሰበር ፋይሉን ለመክፈት በቴክኖሎጂ እገዛ ባለጉዳዮች አዲስ አበባ መሄድ ሳያስፈልጋቸው በአቅራቢያቸው የክልል ዋና ከተማ ተገኝተው ፋይል ሊከፍቱ፣ ሊደመጡ ይችላሉ ሊባል ይቻል ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ በ2007 ዓ.ም ለተከበረው "የፍትሕ ሳምንት" በዓል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረበው ሪፖርት፣ በ2006 ዓ.ም. 709 መዝገቦች፤ በ2007 ዓ.ም. ስድስት ወራት ብቻ ደግሞ 1059 መዝገቦች በኢ-ፋይሊንግ ሥርዓት (e-filing system) እንደተከፈቱ ጠቅሷል፡፡ እንዲህ ያለ አማራጭ የፋይል አከፋፈት ሥርዓት ማመቻቸቱ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱን የሚያስመሰግነው ነው፡፡

ሆኖም ይህ አሠራር በተለያዩ ምክንያቶች የተጠበቀውን ያህል ውጤታማ አይደለም፡፡ አንደኛ አቤቱታው ያስቀርባል፣ አያስቀርብም የሚለውን ለማስወሰን ባለጉዳዩ ራሱ ወይም ጠበቃው አዲስ አበባ መሄዱ የማይቀር ነው፡፡ ሁለተኛ፣ የማኅበረሰባችን ልማድ ሆኖ ዳኛን በቪዲዮ ግንኙነት በኩል ከማነጋገር ይልቅ ባለጉዳዮች በግንባር ቀርበው ዳኛው የሚለውን ከአፉ በቀጥታ

---

[36] በዚህ ረገድ ሊጠቀሱ ከሚችሉት ጥቂቶቹ የሰበር ችሎቱ መዝገቦች ውስጥ የመዝገብ ቁጥር 15410፤ 16273፤ 18307፤ 11924፤ 18581፤ 25526፤ 22275፤ 29692፤ 32545፤ ይገኙባቸዋል፡፡

[37] በአወዛጋቢነታቸው ሊጠቀሱ ከሚችሉ የሰበር ሰሚ ችሎቱ በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ ዙሪያ ከሰጣቸው የሕግ ትርጉሞች ውስጥ የመዝገብ ቁጥር 49152፤ 33314፤36894፤47469 ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

መስማት፣ ብሶታቸውን በአካል ዳኛው ፊት ቀርበው ማስረዳት የበለጠ ተደማጭነትና ተዓማኒነት የሚያስገኝላቸው የሚመስላቸው ወገኖች ቀላል ቁጥር የሚይዙ አይደሉም። ሦስተኛ፣ የቪዲዮ ቴክኖሎጂው በቀጠሮው ዕለት በኃይል እጥረት ወይም በሌላ ቴክኒካዊ ችግር ምክንያት አገልግሎት ስለመስጠቱ ማንም እርግጠኛ ሊሆን ስለማይችል ተለዋጭ ቀጠሮ ለማስቀረት ሲባል አዲስ አበባ በግንባር መቅረብን የሚመርጡ ብዙ ናቸው። አራተኛ፣ በግንባር አዲስ አበባ ቢቀረብም ሆነ አዲስ አበባ መምጣት ሳያስፈልግ በቴክኖሎጂ እገዛ ውሳኔ ቢሰጥ ያው ዞሮ ዞሮ የፍትሕ መጨረሻ ምንጭ አዲስ አበባ ነው የሚል እሳቤ መፍጠሩ አይቀርም።

ሲጠቃለል አሁን በሥራ ላይ ያለው የሰበር ሰበር አሠራር ሰበር ሰሚ ችሎቱን በጉዳዮች ጫና ጠፍሮ ይዞ መላወሻ ያሳጣ፣ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ግዙፉን ደንና ጫካ ማየትና መመርመር ሲገባው፣ በቁጥቋጦዎች ላይ አንዳንዴም በቅጠላ ቅጠል ላይ እንዲያተኩር የሚያደርግ፣ አዲስ አበባ የፍትሕ መነሻና መድረሻ ከተማ ናት የሚል ታሪካዊ አስተሳሰብ መልሶ እንዲያቆጠቁጥ እያደረገ ያለ ክንውን ነው ማለት ይቻላል። ቀጥለን እንዲህ ላለው አሠራር መሠረትና ምክንያት ተደርገው የሚወሰዱትን ነጥቦች እንመረምራለን።

5. ለሰበር ሰበር ወቅታዊ አሠራር የሚቀርቡ ምክንያቶች

በክልል ሕግ መሠረት ታይተው የተወሰኑ የክልል ጉዳዮች በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲመረመሩ እየተደረገ ላለው አሠራር በምክንያታዊነት የሚቀርበው አንዱ ነጥብ በሕገ-መንግሥቱና ሕገ-መንግሥቱን ለማስፈጸም በወጡ የሕግ ሰነዶች የተፈቀደ ድርጊት በመሆኑ ነው የሚል ነው። ለዚህም በዋናነት የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80 በሕገ መንግሥታዊ መሠረትነት ይቀርባል። ይህ አንቀፅ እንደሚከተለው ይነበባል፤[38]

(1) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል።
(2) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልሉ ጉዳይ ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል።
(3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሰው ቢኖርም፤
  ሀ) የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን *ማናቸውንም* የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል። *ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል*። (አጽንኦት የተጨመረ)
  ለ) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን ማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል። *ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፤ …*።[39]

እነዚህን ሦስት የሕገ መንግሥት ንዑሳን አንቀጾች መሠረት በማድረግ በተለይም ለንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) ልዩ ትኩረት በመስጠት የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር የማየት ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ታይቶ ያበቃለትንም ጭምር ሊያስተናግድ ሕገ መንግሥታዊ ሥልጣን አለው የሚል ምክንያት እየቀረበ ነው።

ለዚሁ የክርክር መስመር ማጠናከሪያነት ሕገ መንግሥቱ ሲፀድቅ የተያዘ ቃለ ጉባዔ የሰበር ሰበር እንደሚኖር ያመላከተ በመሆኑ ለድርጊቱ ሕጋዊነት በማጣቀሻነት ይቀርባል። ከዚህም አልፎ ሕገ መንግሥቱ *"ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል"* ስለሚልና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10(3) ደግሞ "የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመደበኛ ችሎት ወይም በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች" ሊያይ

---

[38] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት፤1987 ዓ.ም.፤ *ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ*፤ አንደኛ ዓመት፣ ቁጥር 1 አንቀጽ 80
[39] ዝኒ ከማሁ።

እንደሚችል ስለሚደነግግ፣ ይህ ሐረግ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት እንደ ሥልጣን ምንጭነት ይወሰዳል፡፡

ሁለተኛውና ሌላው ምክንያት ተደርጎ የሚገለፀው አንዳንድ ክልሎች በጠቅላይ ፍርድ ቤቶቻቸው ውስጥ የሰበር ሰሚ ችሎት አላቋቋሙም፣ በዚህ ሁኔታ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ውሳኔ በበታች ፍርድ ቤቶች ሲሰጥ በሰበር ማረም የሚቻልበት ሁኔታ ስለማይኖርና ዜጎች በዚህ ረገድ መፍትሄ ሊሰጣቸው ስለሚገባ የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መኖር ይህንኑ በክልሎች ሊሸፈን ያልተቻለ ክፍተት ለመድፈን ያገለግላል የሚለው ክርክር ነው፡፡

ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ የራሳቸውን የሰበር ችሎት ባቋቋሙ ክልሎች ውስጥም ቢሆን በፍርድ ውሳኔዎች ላይ አልፎ አልፎ የጥራት ጉድለት ብቻ ሳይሆን ጉልህ የሆነ የፍትሕ መጓደል የሚንፀባረቅባቸው ሁኔታዎች ስለሚያጋጥሙ ይህን የመሰሉ ውሳኔዎች በፌዴራል ደረጃ በሰበር እየታዩ ካልተስተካከሉ በቀር በአገር ደረጃ ፍትሐዊነት ማስፈን እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ ስለሆነም የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት እነዚህን በመሰሉ ጉዳዮች ጣልቃ መግባቱ ተገቢ ነው ሲባል ይደመጣል፡፡ በዚህ ዙሪያ በመጨረሻ የሚነሳው ነጥብ በክልል ሰበር ሰሚ ችሎቶች ታይተው የተወሰኑ ጉዳዮችም ቢሆኑ በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ዳግም ተመርምረው በሚወሰኑበት ጊዜ አንድ ወጥና አገር አቀፍ የሕግ አተረጓጎም ሥርዓት እንዲኖር ስለሚያስችል የሰበር ሰበሩ ክንውን ተገቢ ነው ተብሎ ይቀርባል፡፡[40]

ከላይ በምክንያትነት የቀረቡት ሦስት ነጥቦች ያላቸውን ሕጋዊ ተቀባይነትና ተገቢነት ከዚህ ቀጥለን በክፍል 6፣ 7 እና 8+ እንመረምራለን፡፡

6. ሕገ መንግሥቱና ዝርዝር ሕጎች የሰበር ሰበር የሚፈቅዱ መሆን አለመሆኑ

6.1 በክልል ሕጎች መሠረት የሚሰጥ ዳኝነትን የማረም የሰበር ሥልጣን

ለሰበር ሰበር ሥርዓት እንደ ሕገ መንግሥታዊ መሠረት ተደርጎ የተወሰደው የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) ነው፡፡ የሚቀርበው ዋነኛ መከራከሪያ ነጥብም “የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር የማየት ሥልጣን ይኖረዋል” ስለሚል ይህ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ተመርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ያረፈበትንም ይጨምራል የሚል ነው፡፡ ይህንኑ የክርክር መስመር ለማጠናከር የሚቀርበው ሃሳብ ይህ የሕገ መንግሥት ድንጋጌ በረቂቅ ደረጃ ሕገ መንግሥቱን ባፀደቀው በሕገ መንግሥት ጉባዔ ፊት ቀርቦ ውይይት በተደረገበት ግዜ የተያዘው ቃለ-ጉባዔ የሰበር ሰበር ይፈቅዳል በሚል የሚቀርብ ነው፡፡

የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ በዚህ ነጥብ ላይ የተያዘውን ቃለ-ጉባዔ የማየትና የማንበብ ዕድል አጋጥሞታል፡፡ በርግጥ የቃለ-ጉባዔው አዘጋገብ የተናጋሪውን ስምና የተወከለበትን ክልል ወይም ድርጅት እየጠቀሰ እንዲህ የሚል አስተያየት ሰጠ የሚል የቃለ-ጉባዔ አያያዝ ሥርዓት የተከተለ በመሆኑ በእያንዳንዱ ጉዳይ የሕገ መንግሥት ጉባዔውን ሃሳብና ፍላጎት ያንፀባርቃል ወይ? የሚል ስጋት የሚያጭር ጉዳይ አለበት፡፡ ነገር ግን ከቃለጉባዔው በተሻለ መልክ የተደራጀ የሕገ መንግሥቱን አፅዳቂዎች ሃሳብና ፍላጎት የሚያንጸባርቅ (intention of the framers of the Constitution) ሌላ አማራጭ ሰነድ ስለሌለ ቃለ-ጉባዔውን መሠረት ከማድረግ ውጪ ሌላ መፍትሄ አልተገኘም፡፡

በመሆኑም ቃለ-ጉባዔው ከአንድ የሕገ መንግሥት ጉባዔ አባል የቀረበውን አስተያየት በስፋት የመዘገበ ሲሆን አሁን ለተያዘው ነጥብ አግባብነት ያለው የአስተያየቱ ክፍል እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

[40] ሕገ-መንግሥቱን ለማፅደቅ በተደረገው የሕገ መንግሥት ጉባኤ አባላት ውይይት ወቅት ይህ ነጥብ ጎልቶ ወጥቶ ነበር፡፡

> … በክልል ሰበር ችሎት የሚታየውን ጉዳይ የመጨረሻ ነው ማለት አለመሆኑንና ጉዳዮቹን መጀመሪያ የክልል ሰበር ያያቸዋል ማለት እንደሆነ፤ ጉዳዮቹ እዚያም በክልሉ እልባት ካገኙ ጥሩ፣ ያለበለዚያ ግን የፌዴራሉ የሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን እንዳለው፤ ከዚህም ሌላ *የክልል የሰበር ችሎት መኖር የፌዴራሉን የሰበር ችሎት ጫናን እንደሚቀንስ*፣ ጉዳዮችም በትክክል እልባት ሊያገኙ እንደሚችሉ አስረድተዋል።[41] (አጽንኦት የተጨመረ)

በማያያዝም፣ የፌዴራሉ የሰበር ችሎት መኖር አስፈላጊነት *አገር አቀፍና አንድ ወጥ የሕግ አተረጓጎም እንዲኖር ለማድረግ መሆኑን፤ ይህን ለማድረግም የፌዴራል የሰበር ችሎት የግድ መኖር እንዳለበት፤* ስለዚህ በክልልም ሆነ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ካለ ጉዳዩ በሰበር መታየት እንዳለበት ቃለ-ጉባዔው ይገልጻል።[42] (አጽንኦት የተጨመረ)

ከዚህ በላይ ዘርዘር ብሎ ከተቀመጠው የሕገ መንግሥት ቃለ-ጉባዔ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ሕገ መንግሥቱን ያፀደቀው ጉባዔ በክልል ደረጃ በሰበር ሰሚ ችሎት የታየና የመጨረሻ ውሳኔ ያረፈበት ጉዳይ በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎትም ዳግም ሊታይ እንደሚችል ማመልከቱን ነው። እንዲህ በማድረግም የሕገ መንግሥት ጉባዔው አባላት የፌዴራሉን የሰበር ሰሚ ችሎት የሥራ ጫና መቀነስ እንደሚያስችልና በአገር አቀፍ ደረጃም አንድ ወጥ የሕግ አተረጓጎም ሥርዓት ለመፍጠር ያስችላል የሚል እምነት አሳድረው እንደነበር ተመልክቷል።

ነገር ግን እነዚህ ሁለት ምክንያቶች የክልል ጉዳይን በፌዴራል ሰበር ሥርዓት እንዲመረመር ለማድረግ በምክንያትነት ሊቀርቡ የሚችሉ አይደሉም። ምክንያቱም አንደኛ የሰበር ሰበር መኖሩ የፌዴራል ሰበር ችሎትን የሥራ ጫና ይቀንሳል የሚለው አባባል ትክክል አይደለም። ምክንያቱም በክልል ሰበር ቀርቦ ያልተሳካለት ተከራካሪ ወገን ምንም ገደብ ስለሌለው ወደ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት መሄዱ አይቀርም። ፍርድ ቤት በባህርዩ ረቺና ተረቺ የሚለይ ተቋም ስለሆነ የተረታው ቅር መሰኘቱ አይቀርም። በኅብረተሰባችን የተሟጋችነትና መረታትን እንደውርደት የመቁጠር ዝንባሌም እዚህ ላይ ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባዋል። በመሆኑም የሚቀነስ የሥራ ጫና አይኖርም፤ ይልቁንም የሥራ ጫና ይቀነስ የነበረው በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ የተወሰነ ጉዳይ በፌዴራል ሰበር ዳግም ሊመረመር አይችልም ቢባል ነበር።

በሁለተኛ ምክንያትነት የቀረበው ማለትም አንድ ወጥና አገር አቀፍ የሕግ ትርጉም ለመፍጠር የሚለውም ቢሆን የሰበር ሰበር ለማደራጀት አሳማኝ ምክንያት አይደለም። በርግጥ የፌዴራል ሕግ አገር አቀፍና አንድ ወጥ የሕግ ትርጉም እንዲኖረው ማድረግ ይገባል። ነገር ግን የፌዴራል ሕግ ማለት የፌዴራል መንግሥት የሚያወጣቸው ሕጎችና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንጂ የክልል ሕጎችን የሚመለከት አይደለም። የክልል ሕግ ክልላዊ ወጥነት ያለው የሕግ ትርጉም ሊሰጠው ይገባል እንጂ አገር አቀፍና አንድ ወጥ ትርጉም ሊሰጠው ይገባል የሚባል አይደለም። መጀመሪያውኑ የክልል ጉዳይ እንዲሆን የተደረገው ክልላዊ ፋይዳ ብቻ ስላለው ነው። በአንድነት ውስጥ ልዩነት (unity in diversity) ከሚገለፅባቸው የፌዴራል አደረጃጀት ውበቶች አንዱ ይህ ነው። ስለሆነም ስለሰበር ሰበር አስፈላጊነት የቀረበው ሁለተኛ ምክንያትም ተገቢነቱ ለፌዴራል ሕጎች እንጂ ለክልል ሕጎች አይደለም። የፌዴራል ሕግ ከሆነ ደግሞ መጀመሪያውኑ በክልል ሰበር ሊመረመር የሚገባው አይደለም፤ ምክንያቱም በሕገ መንግሥቱ መሠረት በፌዴራል ሕጎች ላይ የመጨረሻ ትርጉም መስጠት ያለበት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው።[43]

በርግጥ የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በክልሉ ውስጥ የሰበር ሰሚ ችሎት ካለ አንድ ጉዳይ በዚያው ክልል በሰበር ሳይመረመር ወደ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብና ሊስተናገድ

---

[41] የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ጉባዔ ቃለ ጉባዔ ጥራዝ 5፣ ገጽ 32።
[42] ዝኒ ከማሁ
[43] የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(1)

አይገባም የሚል አቋም በ2006 ዓ.ም. ወስዷል፡፡[44] በዚህ ጸሐፊ እምነት ግን ተከራካሪ ወገኖች ለክርክራቸው መሠረት ያደረጉት የፌዴራል ሕግን ከሆነ መጀመሪያውኑ የክልል ጉዳይ ስላልሆነ ወደ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት መቅረብ የለበትም ነው፡፡ ምክንያቱም በሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች መሠረት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በክልል ሕግ እንጂ በፌዴራል ሕግ ላይ የመጨረሻ ትርጉም መስጠት አይቻለውም፡፡

የሆነ ሆኖ የሰበር ሰበር እንዲኖር በምክንያትነት የቀረቡት የሕገ መንግሥት ጉባዔው ሁለት ነጥቦች አሁን እየተሠራበት ያለውን የሰበር ሰበር አሠራር የሚደግፉ አይደሉም:: ምክንያቱም አንደኛ በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ታይተው ያበቃላቸው ጉዳዮች በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በድጋሚ እየተመረመሩና ውሳኔ እያረፈባቸው ባለበት ሁኔታ የፌዴራሉን ሰበር ችሎት የሥራ ጫና በመቀነስ ረገድ የሰጡት ጥቅም የለም፡፡ ሁለተኛ አገር አቀፍና አንድ ወጥ የሕግ ትርጉም መኖር ያለበት ለፌዴራል ሕጎች ብቻ ስለሆነ በክልል ሕጎች መሠረት የተስተናገዱትን ጉዳዮች በፌዴራል ሰበር ለመመርመር የሚያስችል ምክንያት አልነበረም፡፡ በመሆኑም በቃለ-ጉባዔው የተመዘገበው ውሳኔና ለውሳኔው መሠረት የሆኑት ምክንያቶች ባልተጣጣሙበት ሁኔታ በወቅቱ በጉዳዩ ላይ በቂ ግንዛቤ አልነበረም ከሚባል በስተቀር የሕገ መንግሥት ጉባዔ አባላት አሁን እየተሠራበት ያለውን የሰበር ሰበር አሠራር ፈቅደውታል፣ ፈቅደውም ተቀብለውታል ማለት አይቻልም፡፡

ሕገ መንግሥቱ የሰበር ሰበር ፈቅዷል ብለን እንኳ ብንነሳ ሕገ መንግሥት በባህርዩ የመሠረታዊ መርሆዎች (fundamental principles) ስብስብ በመሆኑ ለአፈጻጸሙ ዝርዝር ሕግ የሚያስፈልገው ነው፡፡ ለዚህም ይመስላል በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 80(3)(ሀ) ሥር *"ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል"*፤ የሚል ዓረፍተ ነገር እንዲታከልበት የተደረገው፡፡ በመሆኑም ሕገ መንግሥቱን በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም ለዚሁ ዓላማ የታወጁ ድንጋጌዎች ካሉ ማፈላለግ ይገባል ማለት ነው፡፡ ሕገ መንግሥቱ በ1987 የፀደቀ ሲሆን እሱን ተከትሎ ማለትም በ1988 ዓ.ም. የታወጀው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 *"ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል"* ተብሎ በሕገ መንግሥቱ ቃል የተገባለትን ርዕሰ-ጉዳይ ለማሳካት ከወጡት አዋጆች አንዱ ስለመሆኑ ከይዘቱ መናገር ይቻላል፡፡[45]

የአዋጁ አንቀፅ 10 የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትን የሰበር ሥልጣን የሚገልጽ ሲሆን በዚሁ አንቀጽ ውስጥ የፌዴራል ሰበር ችሎቱ "የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት *በመደበኛ ችሎት* ወይም *በይግባኝ አይቶ* የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች" በሰበር የማየት ሥልጣን እንዳለው ተመልክቷል[46] (አጽንኦት የተጨመረ)፡፡ ለሰበር ሰበር መሠረት ተደርገው ከተወሰዱት የሕግ ድንጋጌዎች አንዱና ዋነኛው ይህ ድንጋጌ ነው፡፡

በዚህ ጸሐፊ እምነት በክልል ፍርድ ቤቶች በሰበር ታይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ በፌዴራል ሰበር ለመዳኘት ይህ ድንጋጌ የሚያስችል አይደለም፡፡ ለዚህም ሁለት ምክንያቶች አንስቶ ማየት ይቻላል፡፡ በአዋጁ መሠረት በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይተው በፌዴራሉ ሰበር እንዲታዩ የተወሰኑት ጉዳዮች አንደኛ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመደበኛ ችሎት የመረመራቸው ሲሆን፣ ሁለተኛ ደግሞ በይግባኝ ሰሚነቱ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸው ጉዳዮች ብቻ ናቸው፡፡ በየክልሉ በወጡት የፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጆች መሠረት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዮችን በሦስት ደረጃዎች የማየትና የማስተናገድ ሥልጣን አለው፡፡ አንደኛ በመደበኛ ደረጃ (original jurisdiction) የሚያያቸው ጉዳዮች ይኖራሉ፡፡ ሁለተኛ በይግባኝ ደረጃም (appellate jurisdiction) የሚያያቸው ጉዳዮች ይኖራሉ፡፡

---

44 ኢትዮ-ቴሌኮም ደቡብ ምዕራብና ጋምቤላ ሪጅን እና ወይዘሮ ሳባ መንገሻ፤ የሰበር መዝገብ ቁጥር 94106፤ ቅጽ 16 ይመልከቱ፡፡ ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት በማድረግ የቀረበ የመብት ክርክር ነበር፡፡ በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጀምሮ በክልል የዞን ፍርድ ቤት ቀርቦ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ከጸና በኋላ አመልካቹ ጉዳዩን በቀጥታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሲያቀርበው ሰበር ሰሚው ችሎት መጀመሪያ ወደ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሳይቀርብ ወደዚህ ችሎት መቅረብ አልነበረበትም ብሎ ውድቅ አድርጎበታል፡፡

45 የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ 25/1988 ዓ.ም. *ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ* ሁለተኛ ዓመት፣ቁጥር 13

46 አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10(3) ይመለከቷል፡፡

ከእነዚህ በተጨማሪ በሦስተኛ ደረጃ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሰሚነቱ የሚመረምራቸው ጉዳዮችም አሉ፡፡

አዋጁ በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲስተናገዱ የደነገገው የመጀመሪያዎቹን ሁለት ጉዳዮች ሲሆን የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር ደረጃ አቅርቦ ውሳኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች በተመለከተ በአዋጁ ውስጥ የተመለከተ ነገር የለም፡፡ አዋጁ በዚህ ረገድ ዝምታ በመረጠበት ሁኔታ የሚወሰደው የሕግ ግምት የሰበር ሰበር መፈቀዱን ነው ወይስ መከልከሉን? የሚል ጥያቄ ማንሳትና መመለስ ተገቢ ነው፡፡

ይህንን ለመመለስ የፌዴራል አደረጃጀቱንና የሰበር ሥርዓትን ክንውን ቀረብ ብሎ ማየት ያስፈልጋል፡፡ በፌዴራል አደረጃጀቱ መሠረት መንግሥታዊ ሥልጣን በፌዴራል መንግሥትና በአባል መስተዳደሮች (ክልሎች) የተከፋፈለ ሲሆን በመርህ ደረጃ አንዱ በሌላው ሥልጣን ጣልቃ እንዲገባ የሚፈቀድለት አይደለም፡፡[47] ጣልቃ የሚገባበት ሁኔታ ካለም በሕግ በግልጽ በተመለከተና በልዩ ሁኔታ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ለክልል የዳኝነት አካል የተሰጠ ኃላፊነት በፌዴራል የዳኝነት አካል የሚመረመርበት ሁኔታ የፌዴራልን ለፌዴራል፤ የክልልን ለክልል ከሚለው ሕገ መንግሥታዊ የሥልጣን ክፍፍል አንፃር በልዩ ሁኔታ (exception) የሚታይ ነው:: በሕግ አተረጓጎም መርህ ደግሞ ልዩ ሁኔታዎች በጠባቡ መተርጎም ያለባቸው መሆኑ (exceptions should be interpreted narrowly) ይታወቃል::

ይህንኑ መርህ ከተያዘው ጉዳይ ጋር በተጓዳኝነት ስንመለከተው በአዋጁ ውስጥ በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የሚታዩት ጉዳዮች የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመደበኛ ችሎት ወይም በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸው መሆናቸው የተመለከተ ስለሆነ እነዚህኑ ብቻ ለመመርመር ነው ሥልጣን የተሰጠው ተብሎ መተርጎም ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር የታዩትን በተመለከተ ሕጉ ዝምታ በመምረጡ በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲመረመሩ አልፈቀደም ተብሎ ሊገመት ይገባ ነበር ማለት ነው፡፡

አዋጅ ቁጥር 25/1988 የሰበር ሰበር ለማከናወን የሕግ መሠረት ሊሆን አይችልም እያልን ያለነው በዚህ ምክንያት ብቻ አይደለም፡፡ አንደኛው ተጨማሪ ምክንያት ከአዋጁ ስያሜ የመነጨ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የአዋጁን መግቢያ (preamble) በመመልከት የሚደረስበት መደምደሚያ ነው፡፡ የአዋጁ መጠሪያ "የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ" ነው፡፡ የታወጀውም በፌዴራሉ ፓርላማ ነው፡፡ የአዋጁ የትርጓሜ ክፍልም "የፌዴራል ፍርድ ቤቶች" ማለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ናቸው ብሎ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡[48] ይህም ማለት የክልል ፍርድ ቤቶች ከአዋጁ የተፈፃሚነት ወሰን ውጪ ናቸው ማለት ነው፡፡ በዚህ አዋጅ የክልል ፍርድ ቤቶችን ኃላፊነት ጭምር ለመደንገግ ታስቦ ቢሆን ኖሮ "የፍርድ ቤቶች አዋጅ" ወይም ሌላ ተመሳሳይ አገላለፅ ይጠቀም ነበር፡፡

አሁን ባለን ፌዴራላዊ አወቃቀርና የሥልጣን ክፍፍል መሠረት የፌዴራሉ ፓርላማ ለፌዴራሉ ብቻ እንጂ፣ ለሁሉም ፍርድ ቤቶች (ለፌዴራሉም ለክልሉም) ገዥ የሆነ አዋጅ የማውጣት ሥልጣን የለውም፡፡ የሆነ ሆኖ አዋጅ ቁጥር 25/1988 የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ አዋጁ የወጣበትን ዓላማ የሚደነግገውን የአዋጁ መግቢያ ይዘት በመመርመር የሚደረስበት ነው፡፡ እንደሚከተለው ይነበባል፣ "በ*ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ የዳኝነት ሥልጣን በፌዴራል መንግሥቱና በክልሎች የተከፋፈለ በመሆኑ፤ ሕገ መንግሥቱን መሠረት በማድረግ የፌዴራል ፍርድ ቤቶቹን ሥልጣን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ...*" ይህ አዋጅ ታውጇል ይላል (አጽንኦት የተጨመረ)፡፡[49] በመሆኑም የአዋጁ ዓላማ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ሥልጣንና አሠራር ለመወሰን እንጂ በክልል ፍርድ ቤቶች የሥልጣን ክልል ውስጥ ገብቶ አሠራራቸውን ለመደንገግ ያለመ አይደለም ማለት ነው፡፡

[47] ሕገ መንግሥት አንቀፅ 50(8) ይመልከቱ፡፡
[48] አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 2(4)
[49] የአዋጅ ቁጥር 25/1988 መግቢያ

እዚህ ላይ ምናልባት ሊነሳ የሚችል ተገቢ ጥያቄ አዋጁ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን እንጂ የክልል ፍርድ ቤቶችን የሚመለከት አይደለም ከተባለ ለምን ታዲያ አዋጁ በአንቀፅ 10(3) ሥር "የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት" የሚል ሐረግ አስገባ? የሚል ነው፡፡ ጥያቄው ተገቢ ነው፣ ተገቢ መልስም ሊያገኝ ይገባል፡፡

በኢትዮጵያ የዳኝነት ሥርዓት አደረጃጀት የፌዴራልና የክልል ፍርድ ቤቶች የየራሳቸውን መዋቅር ይዘው በትይዩ (parallel) የተደራጁ ሳይሆኑ የክልል ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን በሕገ መንግሥቱ በተሰጣቸው ውክልና መሠረት ዳኝነታዊ ኃላፊነት እንዳላቸው ቀደም ሲል አይተናል፡፡ በዚህም መሠረት የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን፣ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደግሞ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ይዘው በየክልላቸው የፌዴራል ጉዳዮችን እንዲያስተናግዱ ሕገ መንግሥታዊ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል፡፡ ስለዚህ የክልል ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ሁለት መገለጫዎች አሏቸው ማለት ነው፡፡ በአንድ በኩል የክልል ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችም ቁመና ይዘው ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10(3) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትን የጠቀሰው በክልል ፍርድ ቤትነቱ ለሚያከናውነው የዳኝነት ሥራ ሳይሆን፣ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትነት ሥልጣኑ የሚሠራውን ዳኝነታዊ ሥራ በተመለከተ ነው የሚል እምነት አለን፡፡

በመሆኑም ሕገ መንግሥቱ ሲፀድቅ የሕገ-መንግሥት ጉባዔው አባላት ያንሸራሸሩት ሃሳብም ሆነ፣ ሕገ መንግሥቱንና እሱን ለማስፈጸም የወጡት ሕጎች ቃላት የሰበር ሰበርን እንደማይፈቅዱ ለማሳየት ችለናል ብለን እናምናለን፡፡ ምክንያቱም አንዳቸውም ቢሆን የክልል ሕግ መሠረት ተደርጎ ውሳኔ ያረፈበትን የክልል ጉዳይ እንደገና በፌዴራል ሰበር እንዲታይ ዕድል የሚሰጡ ሆነው አልተገኙም፡፡

በሕግ አተረጓጎም መርህ መሠረት ሕግ ሲተረጎም ቃላቱ ብቻ ሳይሆን መንፈሱንም ጭምር (the spirit of the law) አብሮ መመርመር ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የሕገ መንግሥቱ መንፈስ ምን ይመስላል ብሎ ማየት ይገባል፡፡ የሕገ መንግሥቱን መንፈስ ለመገንዘብ ሕገ መንግሥቱን ለማርቀቅና ለማወጅ ምክንያት የሆኑት ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሁኔታዎች፤ እንዲሁም ሕገ መንግሥቱ ሊፈታ ያለመውን ችግር ወደኋላ ተመልሶ ማየት የግድ ይላል፡፡ በጉዳዩ ላይ አገር አቀፍና አንድ ዓይነት አረዳድ እንደሌለ የሚታወቅ ቢሆንም ኦፊሲየላዊ የሆነው የወቅቱ የሁኔታዎች ግምገማ ከዚህ በታች የተመለከተውን ይመስላል፡፡

ከፌዴራላዊ ሕገ መንግሥቱ መታወጅ በፊት ኢትዮጵያ አገራችን በተማከለ አሃዳዊ መንግሥታዊ አወቃቀር ሥር (unitary and centralized state structure) እንደነበረች የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው፡፡ አጠቃላይ ገዥ ማኅበረሰባዊ ሃሳቡም አንድ አገር፣ አንድ ሕዝብና አንድ ቋንቋ በሚል የሚገለጽ ሆኖ ብዝሃነትን (diversity) ለመቀበል የሚቸገር ነበር፡፡ መንግሥታዊ ሥርዓቱም በነፃና በየወቅቱ በሚደረግና በሚካሄድ የምርጫ ሥርዓት የሚመሠረት ሳይሆን ቀደም ሲል "በመቀባት"ና በዘር ሐረግ፣ ቀጥሎም በጠመንጃ አፈሙዝ መንግሥታዊ ሥልጣን የተያዘበት ወቅት እንደነበረ አይዘነጋም፡፡

በዚህ ኢ-ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ላይ በማመፅ መንግሥታዊ ሥልጣን በነፃ ምርጫ የሚያዝበት፣ የራስ በራስ የማስተዳደር ዕድል የሚፈጠርበት፣ በአካባቢ ባህልና ቋንቋ እንዲሁም በቅርብ ርቀት ፍትሕ የሚገኝበትን ሥርዓት ለማምጣት የተደራጀም ያልተደራጀም፣ በትጥቅ ጭምር የተደገፈ እልህ አስጨራሽ ትግል ተካሂዷል፡፡ የመገንጠል ዓላማ የያዙና ነፍጥ ያነገቡ ነፃ አውጪ ኃይሎችም በየአቅጣጫው መከሰታቸው አልቀረም፡፡ በአጠቃላይ የአገሪቱ ሰላምና አንድነት በከፋ አደጋ ላይ የደረሰበት ወቅት ነበር፡፡

በዚህ ሁለገብ ትግል ምክንያት የተማከለና የአሃዳዊ መንግሥታዊ መዋቅር ጠባቂና ጠበቃ የነበረው ወታደራዊ አገዛዝ በኃይል ከሥልጣን እንዲወገድ እንደተደረገ ይታወቃል፡፡ ከዚያ በኋላ ነው እንግዲህ አሸናፊዎቹ የፖለቲካ ኃይሎች ያለፈው እንዳይደገም፣ አገሪቱ እንደአገር እንድትቀጥል በአንፃሩ ደግሞ የብዙ ሕዝቦች፣ ኃይማኖቶች፣ ቋንቋዎችና ባህሎች አገር መሆኗን

ለማስረገጥ ምንና እንዴት ልናደርግ ይገባል? የሚል ሃሳብ በሕጋዊና ሰላማዊ መድረክ ማብላላት የጀመሩት፡፡

በወቅቱ በመፍትሄነት የተወሰደው መሪ ሃሳብ ከአሃዳዊ መንግሥታዊ ሥርዓት ይልቅ ፌዴራላዊ አደረጃጀትን መከተል ስለነበር፣ ከተማከለ አስተዳደር ይልቅ ሥልጣንን ወደታችኛው የኅብረተሰብ ክፍል በማውረድ ራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር፣ በአካባቢውና በቋንቋው እንዲዳኝ ዕድል የሚፈጥር መንግሥታዊ አደረጃጀት መፍጠር እንደሚገባ መግባባት ላይ ደረሱ፡፡ ይህ መሪ ሃሳብ እንዳይቀለበስ ዘላቂ ሕገ መንግሥታዊ መሠረት መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ አመኑበት፡፡ ነገር ግን ሕገ መንግሥት እንዴትና በማን ይረቀቅ? ይዘቱ ምን ይምሰል? የመሳሰሉትን ለመወሰን ጊዜና ቀጣይ ምክክር የሚጠይቅ ስለነበር የሽግግር ጊዜ ማስፈለጉ አልቀረም፡፡ በመሆኑም የሽግግር ጊዜው መርሆዎች ከሞላ ጎደል በወቅቱ በተቀረፀው ሕገ መንግሥት ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

እንዲያውም ሕገ መንግሥት ማዘጋጀት ያስፈለገው በዋናነት በሽግግሩ ዘመን ለነበረው እምነት፣ ፍልስፍናና አመለካከት አስተማማኝ ዋስትና ለመስጠት ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ መርህ ሕገ መንግሥት ውስጥ ከተካተተ ሕግ አውጪውም ቢሆን እንደ ሌላው አዋጅ በፈለገ ጊዜ ሊያሻሽለው ስለማይችል የተሻለ ዘላቂነትና አስተማማኝነት ይኖረዋል፡፡ ስለሆነም የሕገ መንግሥቱ አጠቃላይ ቅኝት በሽግግሩ ወቅት የነበረውን አስተሳሰብ ከሞላ ጎደል መሠረት ያደረገ ስለነበር በሽግግሩ ወቅት የነበረውን የሕግ ማዕቀፍና አሠራር መመርመር የሕገ መንግሥቱን መንፈስ ለመገንዘብ ይረዳል ተብሎ ይታመናል፡፡

በዚህ ረገድ ለያዝነው ጉዳይ አግባብነት ያላቸውን የሽግግሩ ዘመን ሁለት ሰነዶች መርምረናል፡፡ ከመጀመሪያዎቹ የሽግግሩ ዘመን አዋጆች አንዱ የሆነው "ብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳድሮች ለማቋቋም የወጣ አዋጅ" የሚከተለውን ድንጋጌ ይዞ ይገኛል፡፡ *"በሕግ ተለይተው በማዕከላዊ*[50] *የሽግግር መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሥልጣን ክልል ሥር ከሆኑ ጉዳዮች በስተቀር* ብሔራዊ ክልላዊ የበላይ ፍርድ ቤት በሌሎች በማናቸውም ጉዳዮች ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል" ይላል፡፡[51]

ሌላው የሕግ ሰነድ "የማዕከላዊ ሽግግር መንግሥት ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ" ሲሆን በመግቢያው የብሔር ብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን መብት ተግባራዊ ለማድረግ ይቻል ዘንድ በማዕከላዊው መንግሥትና በብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድሮች መካከል የሥልጣንና ኃላፊነት ድልድል ለማድረግ በወጣው አዋጅ መንፈስ የማዕከላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶችን ማደራጀት አስፈላጊ መሆኑን ካመለከተ በኋላ የማዕከላዊ ጠቅላይ ፍርድ ቤትን የሰበር ሥልጣን ገልጧል፡፡ ይህ ሕግ *የማዕከላዊ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት "የብሔራዊ ክልላዊ የበላይ ፍርድ ቤት ቻርተሩን፣ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ወይም የማዕከላዊ መንግሥት ሕጎችን መሠረት አድርጎ ባከራከረባቸው የመብት የነፃነትና የጥቅም ክልላዊ ጉዳዮች ላይ የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ በሰበር የማየት ሥልጣን"* ያለው መሆኑን ተደንግጎ ነበር፡፡[52]

ከእነዚህ ሁለት የሕግ ሰነዶች መገንዘብ የሚቻለው የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በሽግግሩ ዘመንም ቢሆን በሕግ ተለይተው በማዕከላዊ [ፌዴራል] ጠቅላይ ፍርድ የሥልጣን ክልል ሥር ከሆኑ ጉዳዮች በስተቀር በሌሎች ማናቸውም ጉዳዮች የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ሙሉ ሥልጣን ተጎናፅፈው የነበሩ መሆናቸውን ነው፡፡ በተጨማሪም የማዕከላዊ ጠቅላይ ፍርድ ሰበር ችሎት በክልል ጉዳዮች የነበረው ሥልጣን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራል ሕጎችን

[50] በሽግግሩ ዘመን "የማዕከላዊ የሽግግር መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት" በመባል ይታወቅ የነበረው በአሁኑ ስያሜ "የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት" ነው፡፡ "ብሔራዊ ክልላዊ የበላይ ፍርድ ቤት" ደግሞ በአሁኑ አጠራር "የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት" ነው፡፡

[51] 'የብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳድሮች ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 7/1984'፣ 1984 ዓም *ነጋሪት ጋዜጣ፣* አንቀፅ 25 (1)

[52] የማዕከላዊ ሽግግር መንግሥት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 40/1985 1985 ዓ.ም. *ነጋሪት ጋዜጣ* አንቀፅ 12(1)

ማለትም ቻርተሩን፣ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን እንዲሁም የማዕከላዊ መንግሥት ሕጎችን ተጠቅሞ ጉዳዩን ያስተናገደው ከሆነ ብቻ እንደሆነ ተመልክቷል። ይህም ማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የክልል ሕግ መሠረት አድርጎ ውሳኔ በሰጠበት ጉዳይ ላይ የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን አልነበረውም ማለት ነው።

ስለሆነም የሕገ መንግሥቱ መንፈስም ቢሆን እላይ ለሕገ መንግሥቱ ቃላት ከሰጠነው ትርጉም የተለየ ነገር የለውም። ከዚህ አንፃር የሽግግሩ ዘመንም ሆነ ድኅረ ሽግግር የተደራጀው ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት በዳኝነት ዘርፉ የነበረውና ያለው የፖሊሲ አቅጣጫ "የክልልን ለክልል፤ የፌዴራልን ለፌዴራል" የሚል ሆኖ ዜጎች ፍትሕ ለማግኘት መንከራተት ሳይጠበቅባቸው በአካባቢያቸውና በቋንቋቸው ዳኝነት ማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው፤ ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር፣ የክልል ጉዳያቸውን በክልሉ የአሠራር ሥርዓት መሠረት እንዲወሰን ማስቻል ነው። በአንፃሩ የሰበር ሰበር ሥርዓት መፈጠር ዜጎች እንደጥንቱ ፍትሕ ለማግኘት ወይም ቁርጣቸውን ለማወቅ አዲስ አበባ ድረስ እንዲንከራተቱ በር የከፈተ ክስተት ሆኖ ተገኝቷል። ይህ ግን በዚህ ጸሐፊ ግንዛቤ የሕገ መንግሥቱ ፍላጎት አይደለም። ምክንያቱም የሕገ መንግሥቱ አንዱ ዓላማ ያልተማከለ የፍትሕ አስተዳደር አደራጅቶ የባለጉዳዮችን እንግልት በአጭሩና በቅርብ ለማስቀረት ነበር።

በሁሉም ጉዳዮች የሰበር ሰበር ተግባራዊ ማድረግ ከዜጎች እንግልት ባሻገር ሌላም ፖለቲካዊ ስጋት ይፈጥራል። የክልል መንግሥታት ሕገ መንግሥታዊ መብታቸውን ተጠቅመው የሚያውጇቸውን ሕጎች ለማስፈጸም ሲንቀሳቀሱ ባወጡት ሕግ ይዘት ላይ የፌዴራሉ መንግሥት ደስተኛ ባይሆን እንኳ ሊያቆማቸው አይችልም። ርዕሰ ጉዳዩ በሕገ መንግሥቱ ለክልሎች በተሰጠ የሥልጣን ክልል ውስጥ ከሆነ ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው ነውና።

በክልል ሕግ መሠረት ታይቶ የተወሰነን የክልል ጉዳይ በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በኩል መመረመሩን ከቀጠለ ግን ፌዴራሉ መንግሥት በሕግ አውጪነቱ ሊያሳካ ያልቻለውን ዓላማ በሰበር ሰበር ሥልጣን ማለትም በዳኝነት አካል በኩል የክልል ሕጎችን አፈፃፀም ለመገደብ በር ይከፍትለታል ማለት ነው። ይህ ደግሞ ሕገ መንግሥቱ ያደራጀውን የፌዴራልና የክልሎች የሥልጣን ክፍፍል ስጋት ላይ የሚጥል ከመሆን አልፎ በፌዴራል መንግሥቱና በክልሎች መካከል ለአለመተማመንና ለግንኙነት መሻከር ምቹ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል።

ዜጎች ፍትሕ ለማግኘት መንከራተት የለባቸውም የሚለው አስተሳሰብ ቀደም ሲል በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ለዙፋኑ ቅርበት በነበራቸው ሁለት ሹሞች መካከል የነበረ ውዝግብ የሚያስታውሰን ነው። ውዝግቡ በፊታውራሪ ተክለ ሐዋሪያትና በራስ ካሣ መካከል ነበር። ፊታውራሪ ተክለ ሐዋሪያት "ሕዝቡ በትንሹም በትልቁም ጉዳዩን ለማሰማት ከሩቅ ቦታ ወደ አዲስ አበባ ዙፋን ችሎት እየመጣ ጊዜውንና ገንዘቡን እያባከነ አልፎ አልፎም ትዳርና ቤተሰብ እየፈረሰ ስለሆነ ትናንሹ ጉዳይ እዚያው የሚያልቅበትን ሥርዓት እናመቻች" የሚል ሃሳብ አቀረቡ። በጉዳዩ ላይ ምክክር ይደረግበት ዘንድ አግባብ ወዳለው ኮሚሲዮን (ኮሚሽን) እንዲመራ ተደረገ። የኮሚሲዮኑ አንዱ አባል የነበሩት ራስ ካሣ ይህንኑ ሃሳብ ተቃውመው ያቀረቡት አስተያየት *"እንዲህ ተሆነማ የኛ [ማእከላዊ መንግስት] መብት ሊቀርብን ነው፣ ዳኝነት ከተቀነሰብን እኛ ሌላ ምን ኃይል አለን፣ ለዳኝነት ሲል ነው ሕዝቡ የሚፈልገን በተቀረማ መለስ ብሎ አያየንም"* ብለው እንደነበር በግለ-ታሪክ (ኦውቶባዮግራፊ) ተመዝግቦ ይገኛል።[53]

ለዙፋኑ ቅርብ ከነበሩት ከራስ ካሣ አገላለፅ መገንዘብ የሚቻለው ዙፋን ችሎት የፍትሕ ምንጭ ብቻ ሳይሆን ጠቅላይ ግዛቶቹና ኀብረተ-ሰቡ ለማዕከላዊ መንግሥት ታማኝነታቸውን የሚገልፁበት መድረክም ሆኖ እንዲያገለግል የተደራጀ እንደነበር ነው። በአሁኑ ዘመን ግን ክልሎች በተመሳሳይ መንገድ ለፌዴራሉ መንግሥት ታማኝነታቸውን እንዲገልፁ ይፈለጋል

[53] ይህ ገጠመኝ ራሳቸው ፊታውራሪ ተክለሐዋሪያት ባሳተሙት ግለ ታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል። ፊታውራሪ ተክለሐዋሪያት ተክለ ማርያም (1999)፤ *ኦውቶ-ባዮግራፊ (የሕይወቴ ታሪክ)* (አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ) ገጽ፤412

ተብሎ ስለማይታመን ታማኝነታቸው ለሕገ መንግሥቱ ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡ የሰበር ሰበር መኖር ግን የራስ ካሣ አመለካከት እያቆጠቆጠ ነው ወይ? የሚል ሃሳብ ያጭራል፡፡

6.2 በፌዴራል ሕጎች መሠረት የሚሰጥ ዳኝነትን የማረም የሰበር ሥልጣን

በጽሁፉ መግቢያ እንደተገለፀው አንድ ጉዳይ እንደክልል ጉዳይ የሚቆጠረው ጉዳዩ በሕገ መንግሥቱ የሥልጣን ክፍፍል መሠረት የክልል ተብሎ የተመደበ ከመሆኑ ባሻገር፣ ጉዳዩን ለመዳኘት ጥቅም ላይ የዋለው ሕግም በሕገ መንግሥቱ የሥልጣን ክፍፍል መሠረት በክልል ሕግ አውጪ አካል ሕግ እንዲወጣለት የተመደበ ሲሆን ነው፡፡ በመሆኑም አንድን ጉዳይ የክልል ጉዳይ ነው ለማለት የጉዳዩ ይዘትና ጉዳዩን ለመፍታት ጥቅም ላይ የዋለው ሕግ የክልል መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን የመሰለው ጉዳይ ነው በፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የማይገባው፡፡

ነገር ግን አንዳንዴ ጉዳዩ የክልል ጉዳይ ይሆንና ጉዳዩን ለመፍታት ጥቅም ላይ የዋለው ሕግ የፌዴራል ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ አንድ የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሠራተኛ የእምነት ማጉደል ወንጀል በመፈፀም ይጠረጠርና ክስ ይመሠረትበታል፡፡ በርግጥ ተጠርጣሪው የክልል መንግሥት ሠራተኛ በመሆኑና የወንጀሉ ቀጥተኛ ተጠቂም የክልል መንግሥታዊ አካል በመሆኑ ጉዳዩ የክልል ጉዳይ ነው ሊባል ይችል ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ግን የእምነት ማጉደል ወንጀል ክስ የፌዴራል ሕግ የሆነውን የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች በመጥቀስ የሚመሠረት ክስ ስለሆነ የፌዴራል ባህርይም አለበት፡፡ እንዲህ ዓይነት ቅይጥ ሁኔታ ሲያጋጥም የክልል ጉዳይ ነው ለማለት የሚያስደፍር አይደለም፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግም ከዚህ ጋር ተመሳሳይነት አለው፤ ማለትም ሕጉ የፌዴራል ሆኖ ክርክሩ የሚስተናገደው ግን በክልል ፍርድ ቤቶች ነው፡፡

አሁን ባለው አሠራር እንዲህ ዓይነት ክስ ሲያጋጥም የሥረ-ነገር ሥልጣን ባለው የክልል ፍርድ ቤት ይስተናገዳል፡፡ በይግባኝም ከፍ ወዳለ የክልል ፍርድ ቤት ይኬዳል፡፡ እንዲህ እያለም ወደ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ይቀርባል፡፡ ከዚያም በአንደኛው ወገን አመልካችነት ወደ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የሚቀርብበትን ሁኔታ ማየት የተለመደ ነው፡፡ ይህም የሰበር ሰበር መሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን እንዲህ ባለ ሁኔታ የሰበር ሰበር ስለሚሆን የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀበለው አይገባም ከተባለ የፌዴራል ሕጉ በክልል ፍርድ ቤት የመጨረሻ ትርጉም ተሰጥቶበት ሊያበቃ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የፌዴራሉ ሕግ አገራዊና አንድ ወጥ አተረጓጎም እንዳይኖረው የሚያደርግ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ከሕገ መንግሥቱ አኳያም ሲታይ በፌዴራል ሕግ ላይ የመጨረሻና አስገዳጅ ትርጉም መስጠት ያለበት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው የሚለውን ግልፅ ድንጋጌ የሚጋፋ ይሆናል፡፡[54] በመሆኑም የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት እነዚህን የመሳሰሉ ጉዳዮችን የማስተናገድ መብትም ኃላፊነትም አለው፡፡

ይልቁንም የፌዴራል ሕግ መሠረት ተደርጎ የተወሰኑ ጉዳዮችን በሰበር ማስተናገድ የሌለበት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ነው፡፡ ምክንያቱም ሰበር በባህርዩ በሕጉ ላይ የመጨረሻ ትርጉም የመስጠት ኃላፊነት እንደመሆኑ የክልል ፍርድ ቤት በፌዴራል ሕግ ላይ የመጨረሻ ትርጉም መስጠት አይቻለውም፡፡ ስለዚህ የወንጀል ሕግ፣ የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ፣ የጉምሩክ ሕግ እንዲሁም የንግድ ሕግና የመሳሰሉትን መሠረት በማድረግ ውሳኔ የተሰጠባቸው የክልል ጉዳዮች ቢኖሩ፣ ጥቅም ላይ የዋለው ሕግ የፌዴራል ሕግ ስለሆነ ይህ ሕግ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥና መተርጎም የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን ነው፡፡ ማለትም፣ የክልል ሰበር ሰሚ ችሎቶች እነዚህን የመሳሰሉ ጉዳዮች ሊያስተናግዱ አይገባም፡፡ ስለሆነም፣ በፌዴራል ሕግ የሚዳኙ ጉዳዮችን የክልል ሰበር ሰሚ ችሎቶች እንዳያዩ በማድረግ በዚህ ረገድ የሚከሰተው የሰበር ሰበር ሊቀር ይገባል፡፡

በአጭሩ፣የፌዴራልና የክልል ሰበር ችሎቶች በየሥልጣን ወሰናቸው ቢከለሉ የሰበር ሰበር የማይኖርበትን ሁኔታ መፍጠር ይቻላል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ለሰበር ሰበር መኖር በምክንያትነት የቀረቡትን ሌሎች ነጥቦች ተገቢነት እንመረምራለን፡፡

---

[54] የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 80(1)

7. የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በፌዴራል ሰበር መታረም ይገባዋል የሚለውን በተመለከተ

የአንዳንድ የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሚንፀባረቅባቸው ስለሆኑ በፌዴራል ሰበር መታረም ይገባቸዋል የሚለውን በተመለከተ፣ በርግጥ ከአንዳንድ ክልሎች ወደ ፌዴራል ሰበር ሰሚ የሚቀርቡ ጉዳዮች በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ታይተው የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠባቸው ናቸው ቢባሉም በመለስተኛ የሕግ ባለሙያ እንኳ ታይተው የተወሰኑ ስለመሆናቸው ጥርጣሬ የሚፈጥር ይዘት ይታይባቸዋል፡፡ እንዲያውም አንዳንዴ “የሰበር ሰበር እንኳንም ኖረ” የሚያሰኝ ሁኔታ ይከሰታል፡፡ ከክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ወደ ፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መቅረብ የማይቻል ቢሆን ኖሮ እኮ ይህ የክልል ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዳለ ተፈፃሚ ይሆን ነበር ማለት ነው የሚያሰኝ የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ አልፎ አልፎ ያጋጥማል፡፡

መሠረታዊ የመደመጥ መብት ያልተከበረባቸው፣ ያልተጠየቀ ዳኝነት የተሰጠባቸው፣ የተቆጠሩ ማስረጃዎች ሳይቀርቡና ሳይደመጡ ውሳኔ የተሰጠባቸው፣ መያዝ ያልነበረበት ጭብጥ ተይዞ ውሳኔ የተሰጠባቸውና የመሳሰሉት ብዙ መሠረታዊ ግድፈቶች የተፈፀሙባቸው ውሳኔዎች ያጋጥማሉ፡፡ በመሆኑም ይህ ስጋት ተገቢ ትኩረት የሚጠይቅ ስለመሆኑ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢም ይስማማበታል፡፡ እንዲያውም ለሰበር ሰበር መኖር እንደ ምክንያት ከሚቀርቡት ነጥቦች መካከል ይህ ነጥብ ሚዛን የሚደፋ ይመስላል፡፡

የአንዳንድ ክልሎች የዳኝነት ዘርፍ አቅም ማነስ መፍትሄው ምን ሊሆን ይገባል በሚለው ላይ የሃሳብ ልዩነት ያለ ይመስላል፡፡ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት እያከናወነ ያለውን፣ ማለትም በክልል ሰበር የታዩትን ጉዳዮች ዳግም በሰበር የማየትን አሠራር አጠናክሮ መቀጠል ለችግሩ መፍትሄ እንደሆነ አንዳንዶቹ ሲገልጹ ይደመጣል፡፡ ይህ ግን ፍትሕ የሚገኘው ከፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ነው የሚል የሞራል ልዕልና (moral high ground) የሰነቀ አመለካከት ነው፡፡ ሆኖም እንዲህ ዓይነት አመለካከት ሁልጊዜ ትክክል ነው ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ከወሰነ በኋላም ቢሆን “ኧረ ለማን አቤት ይባላል?” የሚሉ ባለጉዳዮችና ጠበቆች አልፎ አልፎ ያጋጥሙናል፡፡ ከሁሉም በላይ ግን የሰበር ሰበር ጊዚያዊ መፍትሄ ሆኖ ያገለግል እንደሆነ እንጂ ረዥም ርቀት የሚወስደን ዘላቂ መፍትሄ አይሆንም፣ ይልቁንም ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎቱን እማይወጣው የጉዳዮች ጫና ውስጥ የሚከተውና መላወሻ የሚያሳጣው ነው፡፡

ከዚህም አልፎ ሌላው ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባው ጉዳይ የፌዴራል አደረጃጀት ተቀብለን ክልሎች ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ የሚያስችል የፖለቲካ ምህዳር ስንፈጥር በአጭርና በመካከለኛ ጊዜ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የአሠራር መለስተኛ ችግሮችን የመታገስ ዝግጁነት ሊኖረን ይገባል፡፡ ራስን በራስ በብቃት ለማስተዳደር የሚያስችል አቅምና ልምድ በመጓደሉ ምክንያት የሚፈጠሩ ግድፈቶች መኖራቸው አይቀርም፡፡ “ህፃንን ሲወዱ ከነ.....” እንዲሉ፣ ፌዴራል አወቃቀሩ የችግር መፍቻ ቁልፍ ይሰጠናል ያልነውን ያህል አዳዲስ ተግዳሮቶችን ይዞ መምጣቱ ስለማይቀር ራሱን በራሱ እንዲያስተካክል ዕድል ልንሰጠው ይገባል፡፡ ዘላቂ መፍትሄውም አቅም የሚገነባበትንና ልምድ የሚገኝበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር እንጂ አቅምና ልምድ እስኪያዳብሩ ድረስ ራስን በራስ የማስተዳደር መብታቸው “በይደር ይቆይ” ከተባለ መቼም ቢሆን አቅምና ልምድ ሊያዳብሩ አይችሉም፡፡ እንደ አጠቃላይ መርህም ሕገ መንግሥቱን ለመተግበር ሲሞከር የሚያጋጥሙ ችግሮች ለሕገ መንግሥቱ ታማኝ ሆኖና ከዚያው ማዕቀፍ ሳይወጣ ለመፍታት መጣር ይገባል እንጂ ከሃዲዱ መውጣት አደጋ አለው፡፡

መሠረታዊ እውቀቱና የትምህርት ዝግጅቱ ካለ ዳኝነትን ጨምሮ አንዳንድ አቅም የሚገነባው በመለማመድና በተግባር ሂደት (learning by doing) ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መታወቅ ያለበት ጉዳይ የአንዳንድ ክልሎች የአቅም ክፍተት የሚንፀባረቀው በዳኝነት ዘርፍ ብቻ አይደለም፡፡ በሕግ አውጪም ሆነ በአስፈፃሚው ዘርፋቸው ተመሳሳይ ችግር እንዳለ ይታወቃል፡፡ ፌዴራሉ ሕግ አውጪም ሆነ አስፈፃሚው አካል በየሥራ ዘርፋቸው የክልል ምክር ቤቶችንና የክልል ካቢኔዎችን አቅም ለማዳበር የሚበጁ እርምጃዎች ሲወስዱ ይታያሉ እንጂ የክልሎችን ሕገ መንግሥታዊ

ሥልጣን አይነኩባቸውም። የዳኝነት ዘርፉም ቢሆን ተመሳሳይ የመፍትሄ አቅጣጫ ቢከተል የተሻለ ይሆናል።

በዚህ ረገድ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊጫወተው የሚችልና የሚገባው ሚና አለ። በጽሁፉ መግቢያ እንደተገለፀው የክልል ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ከክልል ፍርድ ቤትነት በተጨማሪ እንደቀደም ተከተላቸው በየክልላቸው የፌዴራል መጀመሪያና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶችን ተክተው እንዲሠሩ ሕገ መንግሥታዊ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል። ስለሆነም የክልል ፍርድ ቤቶች አቅም መጎልበትም ሆነ መዳከም በፌዴራል የዳኝነት ዘርፉ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትና ውጤታማነት ላይ የራሱ ጫና ይኖረዋል ማለት ነው። በመሆኑም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከክልሎቹ የዳኝነት አካላት ጋር በሕገ መንግሥት የተሳሰረ የሥራ ግንኙነት ስላለውና ከራሱ የአገልግሎት አሰጣጥም ጋር በቀጥታ የተሳሰረ ስለሆነ አቅማቸውን የማጎልበት ኃላፊነት ይጠበቅበታል።

ይህ ብቻም አይደለም፤ የክልል ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የፌዴራሉን የዳኝነት ሥልጣን ደርበው የሚሠሩ መሆናቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የክልል ዳኞች በክልሉ ምክር ቤት ከመሾማቸው በፊት የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የእጩዎቹ ዝርዝር ቀርቦለት በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ አስተያየት እንዲሰጥባቸው ሕገ መንግሥቱ ሥልጣን ሰጥቶታል።[55] ይህ ዓይነት አሠራር የፌዴራሉ የዳኝነት ተቋም በክልል ዳኞች አቅምና የሙያ ዕውቀት ላይ ሃሳብ ለመስጠት የሚያስችለው ነው።

በርግጥ በፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ተቃውሞ የቀረበበት የክልል ዳኛ ሹመቱ ይቀርበታል ወይ? የተቃውሞው ሕጋዊ ውጤት ምንድን ነው? ለሚሉ ጥያቄዎች ሕገመንግሥቱ መልስ አይሰጥም። እንዲያውም ክልሎች ዳኞቻቸውን ሲሾሙ የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አስተያየት እንዲሰጥባቸው ዕድል አይሰጡም የሚል መረጃም አለ። ይህ እንግዲህ የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ጉዳይ በዜጎችና በመንግሥት ተቋሞች መካከል ባለ ግንኙነት ብቻ ሳይሆን በመንግሥት ተቋሞች መካከል በሚኖር ግንኙነትም ላይ መተግበሩ መረጋገጥ ያለበት ነው። በዚህ ረገድ የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በሕገ መንግሥቱ ለተሰጠው ኃላፊነት መተግበር በብቃት መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል። የሌሎች አገሮች ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቶች የዳበሩትና እየዳበሩ ያሉትም ባለድርሻ አካላት ለሥርዓቶቹ ለተፈፃሚነት በሚያከናውኑት ሕጋዊና ሰላማዊ ትግል ነው። ስለሆነም፣ የክልል የዳኝነት አካላትን የአቅም ክፍተት መድፈን የሚቻለው የአቅም ግንባታ ሥራን በማከናወን ረገድ ዘላቂና አስተማማኝ ተቋማዊ መፍትሄ በመሻት እንጂ ክልሎች የወሰኗቸውን መዝገቦች ዳግም በማየትና በመከለስ (micro-management) ሊሆን አይገባውም።

ከላይ እንደተገለፀው፣ በፌዴራልና በክልል የሥልጣን ክፍፍል ማዕቀፍ ውስጥ ዋናና ወሳኝ የተባሉ ጉዳዮች ማለትም የወንጀል፤ የጉምሩክ፤ የንግድና የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነትን የሚመለከቱ ጉዳዮች በፌዴራል መንግሥት የሥልጣን ክልል ሥር የሚገኙ በመሆናቸው በፌዴራሉ ሰበር የሚመረመሩ ናቸው። ከዚህ ውጪ ያሉት የዕለት ተዕለት የውል፤ የቤተሰብ፤ የውርስና የመሳሰሉት ጉዳዮች የክልል ጉዳዮች ስለሆኑ የፍትሕ አስተዳደራቸው በክልል የዳኝነት ሂደት ላይ ሊያበቃ ይገባል።

ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ አልፎ አልፎ በሕግ ባለሙያዎች አካባቢ በፍትሐ ብሔር ሕግ ውስጥ ያሉት የሕግ ዘርፎች የፌዴራል ሕግ ናቸው ብሎ የመውሰድ አስተሳሰብ አለ። ለዚህ አቋም የሚቀርበው ምክንያት ቀደም ሲል በንጉሡ ዘመን የፍትሐ ብሔር ሕጉ በአገራዊ ሕግ አውጪ አካል የፀደቀ ስለሆነ ክልሎች በሥልጣን ክልላቸው ሥር ለሚወድቁ ጉዳዮች የራሳቸው የክልል ሕግ አውጥተው እስካልሻሩት ድረስ በፌዴራሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደፀደቀ ፌዴራላዊ ሕግ ሊቆጠር ይገባል የሚል ነው። ከዚህ አመለካከት በመነሳትም የክልል የዳኝነት አካላት የፍትሐ ብሔር ሕግ ድንጋጌዎችን ጠቅሰው ውሳኔ ካስተላለፉ በፌዴራል ሕግ መሠረት

[55] የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 81

ዳኝነት እየሰጡ መሆናቸው ታሳቢ ተደርጎ የፌዴራል ሰበር ችሎት በሰበር ሰበር ሥርዓት ጉዳዮቹን ማየቱ ተገቢ ነው የሚል ሃሳብ ይቀርባል፡፡

በዚህ ጸሐፊ አስተያየት ግን በፍትሐ ብሔር ሕግ ውስጥ ያሉት የተለያዩ የሕግ ዘርፎች በሕገ መንግሥቱ የሥልጣን ክፍፍል መሠረት የፌዴራል ጉዳይ ናቸው? ወይስ የክልል? እየተባለ በየሕግ ዘርፉ መመርመር ያለበት እንጂ ሕጉ በማን ወጣ? ሕጉን ያፀደቀው አካል በመንግሥታዊ መዋቅሩ ውስጥ ደረጃው ምን ነበር? እየተባለ ሊሆን አይገባም፡፡ ስለሆነም በፍትሐ ብሔር ሕጉ ውስጥ ያሉት የሕግ ዘርፎች ሁሉም ባይሆኑ አብዛኞዎቹ እንደነ ቤተሰብ፤ ውርስ፤ ንብረት፣ ውልና የመሳሰሉት የክልል ጉዳይ ስለሆኑ የፍትሐ ብሔር ሕጉ የክልል ሕግ እንደሆነ ነው ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው፡፡ ምክንያቱም በሕገ መንግሥቱ ውስጥ በፌዴራሉ ሕግ አውጪ አካል ሕግ እንዲወጣላቸው የተመደቡት የወንጀል፤ የአሠሪና ሠራተኛ፤ የንግድ ሕግና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውጪ ያሉት የሕግ ዘርፎች በመርህ ደረጃ የክልል ጉዳዮች መሆናቸው ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አዋጅ ቁጥር 25/1988 "የፌዴራል መንግሥት ሕጎች" የሚለውን ሲተረጉም "ሕገ መንግሥቱን የማይቃረኑና በሕገ መንግሥቱ ላይ የተጠቀሱትን *በፌዴራል መንግሥቱ ሥልጣን ክልል ሥር ያሉ ጉዳዮችን የሚመለከቱ በሥራ ላይ ያሉ ነባር ሕጎችን ይጨምራል"* ብሎ ተርጉሞታል::[56] በመሆኑም ነባር ሕጎች የፌዴራል ወይም የክልል መሆናቸውን መወሰን የሚቻለው ሕጎቹን ያወጣቸው ማነው የሚለውን በማየት ሳይሆን ሕገ መንግሥቱ በፌዴራልና በክልል ሕግ የማውጣት ሥልጣን ክፍፍል ረገድ የደነገገውን በማየት ነው፡፡

የክልል የተባሉት ጉዳዮች በባህርያቸውና በይዘታቸው አካባቢያዊ (local) ናቸው፡፡ በተለይም የፌዴራሉ ሰበር ችሎት ዳኞች የሁሉንም ክልሎች ባህላዊና ማኅበራዊ ሁኔታዎች በተመለከተ ከክልሉ ዳኞች የላቀ እውቀት ይኖራቸዋል ብሎ መገመት አይቻልም፡፡ በትምህርት ዝግጅትም ሆነ በሥራ ልምድ ረገድ በክልል ውስጥ በዳኝነት ሥራ በተመደቡትና በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ዳኞች መካከል የጎላ ልዩነት የለም:: በመሆኑም ሁሉም ጉዳዮች በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ካልተመረመሩ ፍትሕ አይገኝም ብሎ መከራከር አግባብነት የለውም፡፡

ይልቁንም የፌዴራሉ የሰበር ሰሚ ችሎት ዳኛ የማያውቀውን ባህልና ቋንቋ መሠረት ያደረገውን የክልል ሕግ ሲተረጉም የመሳሳት ዕድሉ ሰፊ ነው፡፡ በርግጥ በአሁኑ ወቅት የክልል ሕጎች ማለት ከሞላ ጎደል ወደ ክልሉ ቋንቋ የተተረጎሙ የፌዴራል ሕጎች ናቸውና የፌዴራሉ የሰበር ዳኛ ሕጉን በመተረጎም ረገድ ችግር አይገጥመውም ልንል እንችል ይሆናል፡፡ ክልሎች የራሳቸውን ሕጎች ባወጡባቸው ርዕሰ ጉዳዮችም ቢሆን የፌዴራሉን ሕግ በሞዴልነት ስለተጠቀሙ ብዙም የተለየ ሕግ የላቸውም፡፡[57] እንዲህ ዓይነት አሠራር ግን አሁን ባለበት ሁኔታ የሚቀጥል ላይሆን ይችላል፡፡

ሕገ-መንግሥት የዛሬ ብቻ ሳይሆን የነገም የበላይ ገዥ ሰነድ (living document) መሆን ስለሚገባው የሕገ መንግሥት አተረጓጎማችንና አፈፃፀማችን ይህንኑ ሊመጣ የሚችል ያልተለመደና አዲስ ክስተት የሚቀበልና የሚያስተናግድ መሆን ይገባዋል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሁሉም የኢትዮጵያ ሕጎች፣ ባህሎችና ቋንቋዎች ላይ የተሟላ ዕውቀትና ግንዛቤ ይኖረዋል ተብሎ ስለማይታመን የፌዴራል ሕግ ተፈጻሚ ከሚደረግባቸው ጉዳዮች ውጭ የክልል ሕጎች በሚተገሩባቸው ጉዳዮች ውሳኔ ላይ ባለሥልጣን (authority) ሊሆን አይቻለውም፡፡

[56] አዋጅ ቁጥር 25/1988, አንቀጽ 2(3) ይመለከቷል::

[57] የቤተሰብ ሕግን በምሳሌነት ብንወስድ ክልሎቹ የየራሳቸው የቤተሰብ ሕግ ያወጁ ቢሆንም ከሞላ ጎደል በሞዴልነት የወሰዱት የፌዴራሉ ሕግ አውጪ አካል ለአዲስ አበባና ለድሬዳዋ አስተዳደሮች ያወጀውን የቤተሰብ ሕግ ስለሆነ ተመሳሳይነት አላቸው፡፡

8. በአንዳንድ ክልሎች የሰበር ሰሚ ችሎት አለመቋቋሙንና የሰበር ሰበር አንድ ወጥ የሕግ አተረጓጎም እንዲኖር ማስቻሉን በሚመለከት

8.1 አንዳንድ ክልሎች የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ያላቋቋሙ ስለሆነ ክፍተቱ በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ሊደፈን ይገባል የሚለውን በተመለከተ

ይህ የክርክር መስመር፣ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ውሳኔዎች ሊፀኑ አይገባም፣ እንዲያውም ሊሻሩ ይገባል፣ ዜጎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት በተፈጸመባቸው ውሳኔዎች መብታቸው ሊጣበብ አይገባም ከሚል መነሻ የሚንደረደር ነው፡፡ ከዚህ እምነት በመነሳት በክልል የበታች ፍርድ ቤቶች የተፈፀሙ መሠረታዊ የሕግ ስህተቶች የሚታረሙበትን የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ክልሉ ካላደራጀ፣ ዜጎች ፍትሕ የማግኘት መብት ስላላቸው የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታደጋቸው ይገባል የሚል ሃሳብ ይቀርባል፡፡ ስጋቱ ተገቢ ነው፣ ትኩረትም ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ ነገር ግን የአስተሳሰቡ ቅኝት ሰበር ከሌለ ፍትሕ የለም የሚል እንደምታ ያለው ይመስላል፡፡ ይህ ብዙ ያነጋግራል፡፡ ለጊዜው ግን ዋና ነጥባችን ስላልሆነ እናልፈዋለን፡፡

የሆነ ሆኖ ይህ የመከራከሪያ ነጥብ ቀደም ብሎ ለነበረ ሁኔታ ያገለግል እንደሁ እንጂ በአሁኑ ወቅት መሠረት ያለው ስጋት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ክልሎችና ሁለቱም የከተማ አስተዳደሮች የየራሳቸው ሰበር ሰሚ ችሎት አቋቁመዋል፡፡ የየራሳቸውን የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ባያቋቁሙ ኖሮም ክፍተቱ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎትን ጣልቃ ገብነት የሚጋብዝ ጉዳይ መሆን አልነበረበትም፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ "የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፣ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡" ተብሎ በፌዴራሉ ሕገ መንግሥት ውስጥ ተደንግጓል፡፡[58]

በዚህ ድንጋጌ መሠረት በክልላቸው ውስጥ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ የሚያርም የሰበር ችሎት የማቋቋም ኃላፊነት ለክልሎች ተሰጥቷል ማለት ነው፡፡ የዚህ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ዓላማና ግብ የዜጎችን ፍትሕ የማግኘት መብት በተሟላ ሁኔታ ለማረጋገጥ አመቺ የዳኝነት ሥርዓት መፍጠር ነው፡፡ በዚሁ ረገድ፣ "በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል መንግሥትና የክልል ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈፃሚና የዳኝነት አካሎች ፍትሕ የማግኘት መብት ያለበትን የሕገ-መንግሥቱ ምዕራፍ (ምዕራፍ 3) የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ እንዳለባቸው" ሕገ መንግሥቱ ደንግጓል፡፡[59]

ይህ የሕገ-መንግሥት ድንጋጌ በክልል የዳኝነት አካላትም ላይ ግዴታ የጣለ ስለመሆኑ አያጠያይቅም፡፡ በመሆኑም የክልል የበላይ ፍርድ ቤቶች የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲያደራጁ ሕገ መንግሥቱ ስለሚያስገድድ ይህንኑ ግዴታቸውን እንዲያከናውኑ ማስገንዘብ ይገባል እንጂ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ፍትሕ በመስጠት ረገድ የተለየ አባታዊ አደራ (paternalistic mind-set) የተጣለበት ይመስል ጉዳዮቻቸውን በሰበር አያለሁ ብሎ መነሳቱ የአሃዳዊ መንግሥት ሥነ-ልቦና (unitary state mentality) ጫና ያለበት ያስመስለዋል፡፡

8.2 የሰበር ሰበር መኖር ሕጎቻችን አንድ ወጥ አተረጓጎም እንዲኖራቸው ያስችላል የሚለውን በተመለከተ

ይህ ነጥብ ቀደም ሲል የተዳሰሰ ሲሆን፣ በአጭሩ በአገር አቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ የሕግ አተረጓጎም እንዲኖር የሚፈለገውና የሚጠበቀው በፌዴራል ደረጃ ተፈፃሚ መሆን ላለባቸው ሕጎች እንጂ ክልላዊ የተፈፃሚነት ወሰንና ክልላዊ ፋይዳ ላላቸው ሕጎች ሊሆን አይችልም፡፡ አገር አቀፍ ተፈፃሚነት የሚኖራቸው ሕጎች ደግሞ የፌዴራል ሕጎች ናቸው፡፡

---

58 የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 80(3)(l)

59 ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 13 (1)

ስለሆነም ክልላዊ ተፈፃሚነት ብቻ ያላቸው ሕጎች በአገር አቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ አተረጓጎም እንዲኖራቸው ይፈለጋል ተብሎ ሊታሰብ አይችልም፡፡ ምክንያቱም መጀመሪያውንም ቢሆን ሕገ መንግሥቱ ጉዳዩን በክልል ጉዳይነት ሲፈርጀውና በክልል ሕግ እንዲወጣለት ሲወስን በአገር አቀፍ ደረጃ አንድ ወጥ አተረጓጎም እንዲኖረው ተፈልጓል ተብሎ ሊወሰድ አይገባም፡፡ ይልቁንም እንደየክልሉ ሁኔታ የተለያየ ሕግና አተረጓጎም እንዲኖር ይፈቅዳል፣ ይቀበላል ማለት ነው፡፡ የፌዴራል ሥርዓት አንዱ ውበቱ ይህንኑ አንድነትና ብዝሃነት ማስተናገድ መቻሉ ነው፡፡ ስለዚህ በአገር ደረጃ አንድ ወጥ የሕግ አተረጓጎም ሥርዓት እንዲኖር የሚፈለገው ለፌዴራል ሕጎች እንጂ የክልል ሕጎችን የሚመለከት ስላልሆነ ይህንን ምክንያት አድርጎ የሰበር ሰበርን ማስቀጠል አይገባም፡፡

ማጠቃለያ: የሰበር ሰበርን ችግር የሚያስቀሩ ሦስት አማራጮች

በፌዴራሉ ሕግ አውጪ አካል ሕግ እንዲወጣላቸው ከተመለከቱት ርዕሰ-ጉዳዮች ውጭ ያሉት ጉዳዮች በሙሉ በክልል ደረጃ ታይተውና ተወስነው ማብቃት እንዳባቸው እንጂ እነዚህ ጉዳዮች በፌዴራሉ ሰበር ሰሚ በድጋሚ እንዲመረመሩ የሕገ መንግሥቱ ቃላትም ሆነ የሕገ መንግሥቱ አጠቃላይ መንፈስ የሚፈቅዱ አይደሉም፡፡ ለሰበር ሰበር የሕግ መሠረት ተደርገው እየተወሰዱ ካሉት ሕጎች አንዱ አዋጅ ቁጥር 25/1988 ነው፡፡ የሕጉ መጠሪያ ስምም ሆነ በመግቢያው የተመለከተው ግብ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አሠራርን ለመደንገግ የወጣ መሆኑን የሚያስረዱ እንደመሆናቸው፣ በክልል ፍርድ ቤቶች ተፈፃሚነት የለውም፡፡ በርግጥ በአዋጁ ውስጥ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በስም ተጠቅሶ የተመለከተ ቢሆንም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ ለሚያከናውነው የዳኝነት ሥራ እንጂ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትነቱ ለሚያከናውነው ተግባር አይደለም፡፡

ከሕገ መንግሥቱና ከሕጉ በመለስ የሰበር ሰበር እንዲኖር በምክንያትነት የሚቀርቡ ነጥቦችም ቢሆኑ ሚዛን የሚደፉ ሆነው አልተገኙም፡፡ ይልቁንም የፌዴራሉን የሥልጣን ክፍፍል ሳይፈታተን (least intrusive means) በሕገ መንግሥቱ ማዕቀፍ ውስጥ ዘላቂና የተሻለ ውጤት ሊያስገኙ የሚችሉ አማራጭ መፍትሄዎች እንዳሉ አሳይተናል፡፡ በመሆኑም አሁን ያለው የሰበር ሰበር አሠራር ሊያበቃ ይገባል፡፡ አሁን እየተሠራበት ያለው የሰበር ሰበር አሠራር እንዲቀጥል ዕድል ከተሰጠው ግን ሕገ መንግሥታዊ ጥያቄ ከማስነሳት አልፎ በፌዴራልና በክልሎች የሥልጣን ክፍፍል ላይ ችግር ይፈጥራል፡፡ ምክንያቱም በሕግ ለክልልና ለፌዴራል ተብሎ የተከፋፈለው መንግሥታዊ ሥልጣንና አንዱ በሌላው ላይ ጣልቃ እንዳይገባ የተቀመጠው ክልከላ በሰበር ሰበር በኩል እንዲሸረሸር ዕድል ይፈጠራል፡፡ ከውጤታማነት አንጻርም ቢሆን ሰበር ሰሚ ችሎቱ ከፍተኛና አገራዊ ፋይዳ ላላቸው ፌዴራላዊ ጉዳዮች ዕውቀቱንና ጉልበቱን መመደብ ሲገባው በክልላዊ ጉዳዮች ተጠምዶ እንዲቀር የሚያደርገው አሠራር ነው፡፡ ይህም ውጤታማ በሆነ መንገድ አስገዳጅና አሳማኝ የሕግ አተረጓጎም የመቅረጽ ተግባሩን ለማከናወን ያለውን ዕድል ያጣብብበታል፡፡

የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት እስካሁን ድረስ በክልል ፍርድ ቤቶች በሰበር ተስተናግደው ፍፃሜ ያገኙትን በክልል ሕግ መሠረት የተዳኙ ክልላዊ ጉዳዮችን በሰበር ሰበር ሲመረምርና ሲወስን የቆየ ቢሆንም፣ በችሎቱ ሥልጣን ረገድ ቀደም ሲል የነበረውን አተረጓጎም የሰበር ችሎቱ ማሻሻል ይችላል፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ አንቀጽ 2(1) እንደተደነገገው፡- "የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት የሚሰጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ የፌዴራል ወይም በክልል ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡ ሆኖም የሰበር ችሎቱ በሌላ ጊዜ በተመሳሳይ ጭብጥ የተለየ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል፡፡"[60]

[60] የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን እንደገና ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 454/1997፣ 1997 ዓ.ም. *ነጋሪት ጋዜጣ* 11ኛ ዓመት ቁጥር 42፣ አንቀጽ 2(1)

በክልል ጉዳዮች የመጨረሻው የሰበር ሥልጣን የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሆኖ ሳለ፣ ይህን በሚጥስ አሠራር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እነዚህን ጉዳዮች ሲያይ የነበረ ቢሆንም፣ ቀደም ሲል ከነበረው አተረጓጎም የተለየ ትርጉም በመስጠት በሰበር ሰበር ምክንያት ወደፊት የሚፈጠሩ ችግሮችን ማስቀረት ይችላል፡፡ በፌዴራል ጉዳዮች ደግሞ የክልል ፍርድ ቤቶች የሰበር ሥልጣን የሌላቸው መሆኑን በመወሰን በዚህ ረገድ የሚከሰተውን የሰበር ሰበር ስህተት ማረም ይችላል፡፡ በእስከ አሁን አሠራሩም ቀደም ሲል በአምስት ዳኞች የሰጣቸውን ጥቂት የሰበር ውሳኔዎች በሰባት ዳኞች ሲሽር ታይቷል፡፡

ሰበር ሰሚ ችሎቱ አሁን ባለው አሠራር የሚቀጥል ከሆነ፣ የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ድርጊት የሕገ መንግሥቱን ቃላትና መንፈስ የተከተለ አይደለም የሚል ጥያቄ ተከራካሪ ወገኖች አንስተው፣ የሰበር ሰበርን ሕገ መንግሥታዊነት በሕገ መንግሥት አጣሪ ጉባዔ በኩል በፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲመረመር ማድረግ የሚችሉ መሆኑ ሁለተኛው የመፍትሄ አቅጣጫ ነው፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በዋናነት የብሔር ብሔረሰቦች ተወካዮች የተካተቱበት አካል ስለሆነ የሰበር ሰበር የክልሎችን ሕገ- መንግሥታዊ ሥልጣን የሚሸረሽር መሆኑን ካመነ ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት መስጠቱ አይቀርም፡፡

ሦስተኛው የመፍትሄ አቅጣጫ የፌዴራሉ ሕግ አውጪ አካል የሕግ ማሻሻያ በማድረግ፣ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ሥልጣን በፌዴራል ጉዳዮችና በፌዴራል ሕግ መሠረት ታይተው በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ የተወሰነ መሆኑን በግልፅ ሊደነግግ መቻሉ ነው፡፡ ይህ የሕግ ማሻሻያ በክልል ሕግ መሠረት ታይተው ከተዳኙ የክልል ጉዳዮች የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ሙሉ በሙሉ እጁን እንዲያነሳ የሚያደርግ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን አሠራር የሚደነግጉት አዋጆች የማሻሻያ ረቂቅ ተዘጋጅቶ የባለድርሻ አካላት ውይይት እየተደረገ ነው፡፡ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በክልል ሕግ መሠረት ታይተው ያበቃላቸውን የክልል ጉዳዮች በሰበር የማስተናገድ ሥልጣን እንደሌለው በአዋጁ ማሻሻያ ከተመለከተ ችግሩ ላንዴና ለመጨረሻ መቋጫ ሊበጅለት ይችላል፡፡ ■

Cassation over Cassation and its Challenges in Ethiopia

Mehari Redae [61]

Summary

The Ethiopian Constitution has allocated judicial power to the Federal Supreme Court and to State Courts on the basis of distinction between "federal matters" and "state matters" in the sense that the former fall within the jurisdiction of the Federal Courts while state matters are adjudicated by the State Courts. However, the Federal Supreme Court Cassation Division has been re-examining cases on a cassation procedure regardless of whether the issue involves a federal or a state matter.

The main theme of this article is that the Federal Supreme Court's re-examination of state matters is against the letters and spirit of the Constitution and has no legal basis. Such practice puts the federal and federated member states'power sharing arrangement at risk. Furthermore, the practice would open flood gates of cases to the bench of the Federal Supreme Court Cassation Division, thereby making it inefficient in terms of timely disposition of cases and quality of decisions. This article underlines that there is neither legal nor factual basis for cassation over cassation in state matters in the present day Ethiopia.

It is further argued that, given its limited resources both human and logistics, it would have been better for the Federal Supreme Court Cassation Division to limit its focus on cases of national and strategic interest rather than on cases having merely local impact. In the author's view, the practice of cassation by the federal court over state matters is a misallocation of meager judicial resources.

The article proposes that the Federal Supreme Court Cassation Division should undertake 'hands-off' principle in cases of state matters. The federal judiciary should rather actively engage itself in capacity building activities of the State Courts, as it is constitutionally mandated to do so, instead of 'micro-managing' their day to day court cases through cassation over cassation.

[61] Mehari Redae, PhD (University of Warwick-UK); LL M (University of Michigan-USA); LL.B (Addis Ababa University-Ethiopia).